DSpace Institution

DSpace Repository | http://dspace.org

Ethiopian Languages and Literature - Amharic | Thesis and Dissertations

2019-11-07

# þÿ è Ó c Ê % - Ó u p C Í Õ + c Ê u ¥ “ - ¨ þÿ ( f õ } Í 5 %

þÿ 5 , @ •

http://hdl.handle.net/123456789/9980

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለአማረኛ ሥነጽሑፍ ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የዓባዊ ሥርዓት ተቃውሞ ምዕራባዊት እና ክልከላ በተሰኙ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ

በ

ሞገስ ሙሉቀን

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

ባሕር ዳር

# የዓባዊ ሥርዓት ተቃውሞ ምዕራባዊት እና ክልከላ በተሰኙ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ


ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የአማርኛ ሥነጽሑፍ ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ

ሞገስ ሙሉቀን

አማካሪ፡- አየነው ጓዱ(ዶ/ር)


ለአማርኛ ሥነጽሑፍ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

ባሕር ዳር

# የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ፊርማ

______________________________ ______________________________

የውስጥ ፈታኝ ስም ፊርማ

______________________________ _________________________

የውጭ ፈታኝ ስም ፊርማ

______________________________ ______________________________

# ማረጋገጫ

የዓባዊ ሥርዓት ተቃውሞ ምዕራባዊትና ክልክላ በተሰኙ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነጽሑፍ ለኤ.ም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ይህ ጥናት ከማንም ያልተኮረጀ የራሴ ሥራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ ስም፡ ሞገስ ሙሉቀን

ፊርማ ___________________

የጥናቱ ማሟያ መርሐ ግብር፡- የአማርኛ ሥነጽሑፍ

ቦታ፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ባሕር ዳር

የጥናቱ ወረቀት የገባበት ቀን፤ ነሐሴ 2011 ዓ.ም

# ምስጋና

በመጀመሪያ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አሟልተህ ሰጥተህ እዚህ ደረጃ ያደረስከኝ ልዑል እግዚአብሔር ክብርና መስጋና ለአንተ ይሁን፡፡

መምህሬ እና አማካሪዬ አየነው ጓዱ (ዶ/ር) የማቀርበውን ጽሑፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል በጥልቀት በማንበብ የተንጋደደውን እያቃናህ ገንቢ አስተያየትና ጥቆማ በመስጠት ለዚህ ውጤት እንድበቃ ስላደረግከኝ ከልብ አመሰግንሃለሁ፡፡

ይህ ጥናት ውጤታማ መሆን እንዲችል ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከፍጻሜው ድርስ ውድ ጊዚያችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ የረዳችሁኝ ትጓደድ እድሜ፣ በላይነህ መዝገቡና አብዩ ተክለማርያም ፈጣሪ ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ ከማለት ውጭ ሌላ የምገልጽበት ቃል የለኝም፡፡ በተጨማሪም በስልክም ሆነ በአካል ሥራህ ከምን ደረሰ እያላችሁ ስትጠይቁኝና ስታበረታቱኝ የነበራችሁ ውድ ጓደኞቼ ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ይህን የትምህርት ዕድል በማመቻቸት እንዲሁም የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ያስተማሩኝን የአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድቤት እና ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲን በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ iv

ምዕራፍ አንድ፦ መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 6

1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 6

1.5. የጥናቱ ፍይዳ ........ 7

1.6. የጥናቱ ገደብ እና ውስንነቶች ........ 7

1.7. የጥናቱ ሥነዘዴ ........ 7

1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 8

ምዕራፍ ሁለት፦ የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ ........ 9

2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ ........ 9

2.1.1. የአንስታይ ሂስ ምንነት ........ 9

2.1.2. ሴቶችና ሥነጽሑፍ ........ 10

2.1.3. ዓባዊ ሥርዓት ........ 13

2.1.3.1. ሴቶች እና ኢኮኖሚ ........ 14

2.1.3.2. ሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳዩች ........ 16

2.1.3.3. መደብ ........ 18

2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ ........ 21

ምዕራፍ ሦስት፦ ትንተና ........ 24

3.1. የልቦለዶቹ አጽመ ታሪክ ........................................................................ 24
3.2. ትንተና ........................................................................ 25
3.2.1. ዓባዊ ሥርዓት ........................................................................ 25
3.2.1.1. የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ድርሻ ........................................................................ 30
3.2.1.2. የሴቶች ማህበራዊ ተሳትፎ ........................................................................ 33
3.2.1.3. የመደብ ተጽዕኖ ........................................................................ 40
ምዕራፍ አራት፦ ማጠቃለያ እና መደምደሚያ ........................................................................ 47
4.1. ማጠቃለያ ........................................................................ 47
4.2. መደምደሚያ ........................................................................ 48
ዋቢ ጽሑፎች ........................................................................ 50

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የዓባዊ ሥርዓት ተቃውሞ በአሰፋ በቀለ *ምዕራባዊት* (2004) እና በዮርዳኖስ ሽፈራው *ክልክላ* (2010) ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ምን ይመስላል የሚል ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ የተመረጡትን ልቦለዶች ከአንስታይ ሂስ ንድፈ ሃሳብ አንጻር መመርመር ነው። አጥኚው ዋና ዓላማውን ለማሳካት በልቦለዶቹ ውስጥ የሚስተዋሉ የሴትነት ጉዳዮች በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ እና በመደብ ልዩነት ከዓባዊ ሥርዓት አንጻር መተንተን የሚሉት ደግሞ ንዑሳን ዓላማዎች ናቸው። አጥኚው እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት ሰነድ ፍተሻን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የተጠቀመ ሲሆን የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ የጭብጥ ትንተና ነው። እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ዘዴዎች በመጠቀም በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች በኢኮኖሚያዊ እና በማህበራዊ ጉዳዮች የተሰጣቸው ድርሻ ምን እንደሚመስል እንዲሁም ከመደብ አንጻር በምን መልኩ እንደቀረቡ ትንተና አድርጓል። በትንተናው መሰረትም ሴቶች ከኢኮኖሚ አንጻር በተለያዩ መስኮች በመሰማራት ውጤታማ የሆኑና ከዚህ ቀደም የነበረውን የዓባዊ አስተሳሰብ የጣሱ ሆነው ተገኝተዋል። በማህበራዊ ተሳትፏቸውም በሁሉም ዘርፍ በንቃት የሚሳተፉና በሚሳተፉባቸው ተግባራትም የመሪነት ሚና ተላብሰው የቀረቡና ቀድሞ የነበረውን ኋላቀር አስተሳሰብ በጽኑ የሚቃወሙና ዓባዊ አስተሳሰቡን ጥሰው ሴቶች በማንኛውም ዘርፍ ስኬታማ መሆን እንደሚችሉ በተግባር ያሳዩ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል። ከመደብ አንጻር ሲታዩ ደግሞ በልቦለዶቹ ውስጥ ወንዶች በሴቶች ላይ ሳይሆን፣ ሴቶች በወንዶችና ሴቶች በሴቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ መሆናቸውን ትንተናው አሳይቷል። በአጠቃላይ ጥናቱ በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች የቀረቡበት መንገድ በጠንካራነት የተሳሉና ከዚህ ቀደም የነበረውን ዓባዊ ሥርዓት በመጣስ የቀረቡ መሆናቸውን አሳይቷል።

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር በማህበራዊ ህይወቱ የሚገጥሙትን ጥሩ እና መጥፎ ክስተቶችን የሚያስተናግድ ፍጡር ነው፡፡ ክስተቶችን በመቃወምም ሆነ በመቀበል ስሜቱን የሚገልጽባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ *ሥነጽሑፍ* ነው፡፡ በዚህም የሰው ልጅ አስተሳሰቡን፣ አመለካከቱን፣ ፍልስፍናውንና መሰል ጉዳዮችን ይገልጽበታል፡፡ *ሥነጽሑፍ* ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚያካትት ነው፡፡ ስለሆነም ደራሲያን የማህበረሰቡን ጉዳዮች ጥበብን በማላበስ አስውበው ያቀርቡበታል፡፡ በ*ሥነጽሑፍ* ውስጥ የሚቀረቡት ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ደግሞ በተለያዩ የ*ሥነጽሑፍ* ሂስ አይነቶች ሊፈተሹ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው የአንስታይ ሂስ ሲሆን በዚህ የሂስ አይነትም ሴቶች በእያንዳንዱ ዘርፍ ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ይፈተሽበታል፡፡ የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫም በአሰፋ በቀለ *ምዕራባዊት (*2004) እና በዮርዳኖስ ሽፈራው *ክልክላ* (2010) *የተሰኙ* ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የዓባዊ *ሥርዓት* ተቃውሞ በምን መልክ ቀርቧል፤ የሚለውን መመርመር ነው፡፡ *ክልክላ* የዮርዳኖስ ሽፈረው የመጀመሪያ *ሥራዋ* ሲሆን ደራሲዋ ሌላ ተጨማሪ *ሥራዎች* እንደሌሏት ከአደረኩት ዳሰሳ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ሌላው አሰፋ በቀለ ሶስት ረጅም ልበለዶች ያሉት ሲሆን ድረሰቶችም *ያልታበሱ እንባዎች፣ አፈላማ* እና የዚህ *ሥራ* ትኩረት የሆነው *ምዕራባዊት* የተሰኙት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት የደራሲው *ሥራዎች* በጥናቴ ላይ ያልተካተቱበት ምክንያት ይዘውት የተነሱት ጭብጥ ከሴትነት ርዕሰ ጉዳዩች ጋር አብረው ሊሄዱ ባለመቻላቸው ነው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የአንስታይ ሂስ በተለያዩ የ*ሥነጽሑፍ ሥራዎች* ውስጥ ሴቶች እንዴት ቀርበዋል የሚለውን የሚፈትሽ የሂስ አይነት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Tyson (1999) እንደገለጸችው አንስታይ ሂስ ሰፋ ባለ መልኩ ሲታይ *ሥነጽሑፍ* እና ሌሎች የባህል ዘርፎች የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና *ሥነልቦናዊ* ጭቆናዎችን መፍትሄ የመስጠት ሂደትን ወይም የሴቶችን ጭቆና የሚያባብሱ ሁኔታዎችን የሚመረምር የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ታብራራለች፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው አንስታይ ሂስ በአንድ የ*ሥነጽሑፍ ሥራ* ውስጥ ሴቶች በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ በመገምገም፣ የወንዶችን የበላይነት

በመቃወም የሴቶችን ጭቆና ማስቀረት፣ እንዲሁም ዓባዊ ሥርዓት በሴቶች ላይ የሚያደረሠውን ተጽዕኖ መቀነስ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

አንስታይ ሂስ የሴቶችን መድሎ፣ በደልና ጭቆና እንዲሁም የመደብ ልዩነትን ማለትም የወንዶችን የማኅበራዊ፣ የፖለቲካዊ እና የኢኮኖሚያዊ የበላይነት በመቃወም የማኅበረሰቡን የለውጥ ሂደት በሥነጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ በምን መልክ ቀርቧል፤ የሚሉትን ሀሳቦች ትኩረት አድርጎ ይፈትሻል፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ Warhol and Hernd (1991) እንደገለጹት በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ሴቶች ተጨቁነው የቆዩ ሲሆን ይህን ጭቆና ለማስቀረት ወይም ለመታገል ደግሞ አንስታይ ሂስ ትልቅ ሚና ይጫዎታል፤ በማለት ያብራራሉ፡፡ ይህ ሃሳብ የሚያስረዳው ሴቶች በቀደምት የሥነጽሑፍ ሥራዎች ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች ተገልለውና ተጨቁነው የቆዩ መሆናቸውን ነው፡፡ አንስታይ ሂስ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ የወንዶችና የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ የሚሰራ የጥናት መስክ ነው፡፡

የአንስታይ ሂስ ዋና አላማ የተጨቆኑ ሴቶችን ከወንዶች እኩል በማሳተፍ ያላቸውን ክፍተት መቀነስ ወይም ማሻሻል ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Tyson (2006) እንደገለጸችው የአንስታይ ሂስ አራማጆች ለዓባዊ ሥርዓት ርዕዮተ ዓለም የተቃውሞ ምላሽ አላቸው በማለት ታስረዳለች፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የዓባዊ ሥርዓት ርዕዮተ ዓለም የወንዶችን የበላይነት ብቻ በማመን ሴቶችን የበታችና አቅመ ቢስ አድርጎ ሥለሚያስብ ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶች ይህንን ኢ-ፍትሃዊ የሆነ አስተሳሰብ በመቃወም ምክንያታዊ በሆነ መንገድ በሥነጽሑፍ ውስጥ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሴቶች ንቅናቄ ጽንስ ሀሳብን በተመለከተ በርካታ ጽሑፎች ተጽፍዋል፡፡ ከነዚህ መካከል በ*Mary Wollstonecraft (1792) The Vindication of the Rights of Women በሚል* ጽሑፍ እንደተጀመረ Tyson (2006) ታስረዳለች፡፡ ጽሑፉም ሴቶች በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባ ሚና ምን መምሰል እንዳለበት ያትታል፡፡ በተመሳሳይም *Virginia Woolf* (1929) *ARoom of One's Own* በተሰኘው መጽሐፍ ሴቶች በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ እኩል ተጠቃሚ ሲሆኑ እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡

ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች እንደሚያመለክቱት በአለፉት ዘመናት ሴቶች እና ወንዶች በታሪክ ውስጥ እኩል መብት ያልነበራቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን ኢፍትሃዊነት

ለማስወገድ ሴቶች በየጊዜው ትግል አድርገዋል። የትግላቸው ውጤትም ፍሬ አፍርቶ ሴቶች መብታቸውን እንደሚያስከብሩ እና ከወንዶች ጋር እኩል እንደሚሆኑ እንቅስቃሴያቸው ያሳየ ነበር። ይህ የሴቶች እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ እንኳን ባይባልም በተወሰነ መልኩ ዓባዊ ሥርዓትን በማስወገድ የሴቶችን እኩልነት በማስፈን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የሴቶች ንቅናቄ በሰው ልጆች ነጻነት ዙሪያ አይነተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ እንቅስቃሴ አጠቃላይ የሴቶችን አቅም ከማሳደግ አንጻር አለማቀፋዊ የትግል ሂደትን የሚያሳይ ነው። ስለሆነም የሴቶች ንቅናቄ ጽንስ ሀሳብ የወንዶችን የበላይነት መዋጋትና ሴቶች ከወንዶች ጋር ያላቸውን እኩልነት ማስፈን ነው። ይህንን ሃሳብ በተመለከተ Tyson (2006) እንደሚከተለው ታስረዳለች።

> በዓባዊ ሥርዓት አስተሳሰብ ወንዶችን እንደምክንያታዊ፣ ጠንካራና ወሳኝ በማለት ሲገልጽ ሴቶችን ደግሞ እንደ ስሜታዊ፣ በኢኮኖሚ ደካማ፣ ቤተሰብ ተንከባካቢ እና ተገዢዎች ናቸው በማለት ይገልጻል። እነዚህ የሥርዓተ ፆታ ልዩነቶች ዛሬም ድርስ ይስተዋላሉ። ለምሳሌ ሴቶች በአመራርነት ቦታና በውሳኔ ሰጭነት ላይ ያላቸው ሚና አናሳ ነው። እንዲሁም በትምህርት አካዳሚ ውስጥ ሴቶች ሥራ ማግኘት ቢችሉ እንኳን ሂሳብ እና ምህንድስና ሙያ እንደሌላቸው ተደርገው ይቆጠራሉ።

ከጥቅሱ የምንረዳው በዓባዊ ሥርዓት ርዕዮተ ዓለም በተለያዩ ዘረፎች ሴቶች ከወንዶች በተለየ ደካማ እና የመስራት ብቃትና ሙያ የሌላቸው ተደርገው በመቆጠር እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ተደርገው የቆዩ መሆኑን ያሳያል። ከዚህ ባለፈም የሚሰማሩባቸው የሥራ መስኮችም ዝቅተኛ እና አይችሉም በሚል የተገደቡ ናቸው።

Wood (2012) እንደምትገልጸው የጾታ አድሎአዊነት በማኅበረሰብ ውስጥ የተፈጠረ ክስተት መሆኑን ተረድተን በለውጥ ሀይሎች ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ይገባል። ወንዶችን በኢኮኖሚ ደረጃ የበላይ አድርጎ መውሰድ ጤናማ አስተሳሰብ አይደለም። በማንኛውም ዘርፍ ላይ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የመስራት አቅም አላቸው። ነገርግን በዓባዊ ሥርዓት አማካኝነት በእነዚህ ዘርፎች አድሎ ተደርጎባቸው ቆይቷል። ሥለሆነም ይህንን ተግባር በመቃወም የጾታ እኩልነት እንዲተገበር አንስታይ ሂስ በሴቶች ላይ ትኩርት አድርጎ ይሰራል። ከዚህ በተቃራኒ የሚገለጸው ዓባዊ ሥርዓት ሲሆን ይህም ወንዶችን በተለያዩ ጉዳዮች የበላይ አድርጎ የሚመለከት ርዕዮተ

ዓለም ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Julian Wolfreys, Ruth Robbinsand, Kenneth Womack (2006) እንደገለጹት፡-

> Patriarchy, Literally the rule of the father Patriarchy is the name given to the whole complex system of male dominance by which most societies are run now and were run in the past. Patriarchy includes the systematic exclusion of women from rights of inheritance, to education, the vote, equal pay, equal rights before the law; it also includes the ways in which even more liberal regimes tend to leave women out of structures of power even when they claim to be regimes based on equality.
>
> ዓባዊ ሥርዓት ማለት ወንዶችን የበላይ ሴቶችን ደግሞ የበታች አድርጎ ሲቆጥር ለነበረውና አሁንም በመቀጠል ላይ ያለው ኋላ ቀር አስተሳሰብ የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡ ዓባዊ ሥርዓት የሚያካትተው የሴቶችን እኩል ውርስ የማግኘት መብት የሚከለክል፤ በትምህርት፣ በምርጫ፣ ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ፣ በማህበራዊ መዋቅርና በስልጣን በአጠቃላይም በእኩልነት መብት ላይ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያገለለ ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ የሚያመለክተው ዓባዊ ሥርዓት ወንዶችን የበላይ ሴቶችን ደግሞ የበታች አድርጎ ሲቆጥር ለነበረውና አሁንም በመቀጠል ላይ ላለው ኋላ ቀር አስተሳሰብ የተሰጠ መጠሪያ መሆኑንና ሴቶችን በትምህርት፣ በምርጫ፣ ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ በአጠቃላይም ሴቶችን እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረገ ኋላ ቀር አስተሳሰብ መሆኑን ነው፡፡

Tyson (2006) እንደገለጸችው በዓባዊ ሥርዓት ውስጥ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የማየት ልማድ ባህላዊ እንጅ ተፈጥሯዊ አይደለም፡፡ ይህ አመለካከት ዛሬም ድረስ በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ይንጸባረቃል፡፡ ዓባዊ ሥርዓት በሴቶች ላይ አድሎ ሲሰራ የቆየው ከማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ባሻገር በቋንቋ አማካኝነትም የበታች መሆናቸውን በመግለጽ ነው፡፡ ይህ ማለት ወንዶችን በከፍተኛ ደርጃ የሚያሞካሹ ቃላት ሲጠቀሙ ለሴቶች ደግሞ ደካማነትንና የበታችነት የሚያመለክቱ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡ ሌላው ወንዶች ሲባልጉ ወይም ስህተት ሲሰሩ እንደጀግንነት ሲቆጠር፤ ሴቶች የሚሰሩትን ተግባር ግን አንደጥፋት የሚቆጠሩት በርካታዎች ናቸው፤ በማለት ታስረዳለች፡፡

በተጨማሪም ከሥነጽሑፍ *ሥራዎች አንጻር* Selamawit (2002) Ruthven (1984) ጠቅሳ እንስት ጸሕፍያን ከተሳካላቸው እንደ እድለኛ ሲቆጠሩ ወንዶች ደግሞ እንደ ጀግና ይቆጠራሉ በማለት ታስረዳለች፡፡ ይህ ሀሳብ የሚያሳየው ደራሲያን ያላቸውን አካዳሚያዊ እውቀት ወይም ችሎታ ያገናዘበ ሳይሆን በጾታቸው ብቻ የሚፈረጁ መሆናቸውን ነው፡፡

ከላይ የተነሱት ሃሳቦች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ ዓባዊ *ሥርዓቱ* የወንዶችን የበላይነት የሚያሳይ ሲሆን አንስታይ ሂስ ደግሞ ይህንኑ በመቃወም የሴቶችን እኩልነት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረቱን በሥነጽሑፋዊ *ሥራዎች* ላይ አድርጎ የሚሰራ ነው፡፡ ይህም ጥናት የአንስታይ ሂስ ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ በ(2004) ዓ.ም በአሰፋ በቀለ በተጻፈው *ምዕራባዊት እና* በ(2010) ዓ.ም በዮርዳኖስ ሽፈራው በተጻፈው *ክልክላ* በተሰኙ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የዓባዊ *ሥርዓት* ተቃውሞ ምን ይመስላል የሚለውን የሚፈትሽ ይሆናል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በሥነጽሑፍ *ሥራዎች* ውስጥ አሁንም ድረስ ሴቶችን በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ዘርፎች ውስጥ የሚሰጣቸው ቦታ ዝቅተኛ ነው የሚለውን አስተሳሰብ በርካቶች የሚጋሩት መሆኑ እና ይህም አስተሳሰብ እየተሻሻለና እየተቀየረ አለመምጣቱ ለምን የሚለውን ጥያቄ ያጭርብኛ ነበር፤ ይህንንም የበለጠ ለማረጋገጥ በሴቶች ዙርያ የተሰሩ የተለያዩ ጥናቶችን ዳሰሳ ሳደርግ ሀሳቡን የሚጋሩ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ከነዚህ መካከልም የአጋረደች ጀማነህ (-) "ሴትነትና እናትነት በፀሃይ መላኩ ልቦለዶች ውስጥ" የሚል ሲሆን በጥናቷም በልቦለዶቹ ውስጥ ያሉ ሴት ገጸባህሪያት ሀይል አጠው በወንዶች የበላይነት ሲመሩ አሳይታለች፡፡ *በቃሳ*፣ በ*አንጉዝ* እና *በቢስ ራሔል* ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ሴት ገጸባህሪያት በአስተሳሰብና በኢኮኖሚ የወንዶች ጥገኛ መሆናቸው ሲሆን የመጨረሻ ግባቸውም አግብቶ ልጅ በመውለድ ልጆችን የመንከባከብ ደረጃ ላይ መድረስ መሆኑን ከልቦለዶቹ በማስያነት አቅርባለች፡፡

ሌላው ብርሃን አሰፋ (2009) "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል ጥናቱ ወንዶች የበላይነታቸውን ለማስቀጠል ተረቶችን ተንትኖ ሴቶች በስልጣን ደረጃ ቦታ የሌላቸው መሆኑን ገልጿል፡፡ በተመሳሳይም እስክንድር ሀይሉ (2008) ደግሞ "የሴቶች ሚና እና መስዋትነት በፖለቲካዊ ተውኔቶች እና ፊልሞች ውስጥ" በሚል ርዕስ በአካሄደው ምርምር ውስጥ የወንድ ገጸባህርያት የበላይ ሴቶች ደግሞ የበታች ተደርገው መሳላቸውን አሳይቷል፡፡ ምንም እንኳ ከላይ የቀረቡት ተመራማሪዎች ሴቶች በማኅበራዊ፣

በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች ዝቅተኛ ድርሻ የተሰጣቸውና ጭቁን ገጸባህሪያት በመሆን የተሳሉ ናቸው፤ በማለት የገለጹ ቢሆንም ከዚህ በተለየ መልኩ በተመረጡት ልቦለዶች ላይ የሴቶች ሚና ሊኖር ይችል ይሆን የሚለው ቀዳሚ አነሳሽ ምክንያቴ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ባደረኩት ዳሰሳ ክልክላና ምዕራባዊት በተሰኙት ረጅም ልቦለዶች ላይ የተደረገ ጥናት ባለመኖሩ ነው፡፡

## 1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚመልሳቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ልቦለዶቹ የዓባዊ ሥርዓት ርዕዮተ ዓለምን ያጠናክራሉ ወይንስ ይቃወማሉ?
2. በልቦለዶቹ ውስጥ የሴቶች ማህበራዊ ተሳትፎ ምን ይመስላል?
3. በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ድርሻ በምን መልክ ቀርቧል?
4. በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች ከመደብ አንጻር በምን መልኩ ቀርበዋል? የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ የዓባዊ ሥርዓት ተቃውሞ *ምዕራባዊት* እና *ክልክላ* በተሰኙ ሁለት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ምን ይመስላል የሚለውን መመርመር ነው፡፡

ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ተቀርጸዋል፤

1. የዓባዊ ሥርዓት ርዕዮተ ዓለምን ልቦለዶቹ ያጠናክራሉ ወይንስ ይቃወማሉ የሚለውን መፈተሽ፣
2. በልቦለዶቹ ውስጥ የሴቶች ማህበራዊ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ማሳየት፣
3. በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ድርሻ በምን መልክ እንደቀረበ መተንተን፣
4. በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች ከመደብ አንጻር በምን መልኩ እንደቀረቡ ማሳየት የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ፍይዳ

ይህ ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ ለደራሲያን፣ ለሴቶችና ለተመራማሪዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፤

- ሴቶች እድሉን ቢያገኙ ከወንዶች እኩል መስራት እንደሚችሉ ጥናቱ ያሳያል፡፡
- ይህን ጥናት ለሚያነቡ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለሴቶች ያላቸውን የተዛባ አመለካካት እንዲቀይሩ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡
- ወደፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኝዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ገደብ እና ውስንነቶች

ይህ ጥናት *ምዕራባዊት (2004)* እና *ክልክላ (2010)* በተሰኙ ረጅም ልቦለዶች ላይ የተወሰነ ነው፡፡ አጥኚው በእነዚህ ልቦለዶች ላይ ያተኮረበት ምክንያት ሴቶች በዋና ገጸባህሪነት ተስለው የቀረቡ ስለሆነ ለርዕሰ ጉዳዩ በቂ መረጃ ይሰጡኛል ብሎ ስላሰበ ነው፡፡ ጥናቱም አንስታይ የሥነጽሑፍ ንድፈ ሃሳብን መሰረት ያደረገ ሲሆን፣ የሚዳሰሱት ነጥቦችም ዓባዊ ሥርዓት ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ እና ከመደብ አንጻር እንዴት ተንጸባርቋል በሚሉት ነጥቦች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ሌሎች የደራሲዎች ሥራዎች ያልተካተቱበት ምክንያት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ስለማይሄዱ እና የተመረጡ ልቦለዶች በቂ ናቸው ብዬ በማሰቤ ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ሥነዘዴ

የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ ሲሆን ንድፈ ሃሳባዊ መታገያውም feminist Theory (የአንስታይ ሂስ)ን መሰረት በማድረግ ለምርምር በተመረጡት ድርሰቶች ላይ የቴክስት ትንተና ያደርጋል፡፡ አጥኚው ትንተናውን የሚያካሂደው ከልቦለዶቹ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ሲሆን መረጃ ለመሰብሰብ ደግሞ ሰነድ ፍተሻን ተጠቅሟል፡፡ ይህን የመረጠበት ምክንያትም ጥናቱን ሲያከናውን መረጃዎቹን የሚሰበስበው ልቦለዶቹን በጥልቀት በማንበብ እና ከጥናት ርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችንና ንድፈ ሃሳቦችን በመፈተሽ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው፡፡

መረጃዎቹን በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ የጭብጥ ትንተና የሚያደርግ ሲሆን ይህን የመረጠበት ምክንያትም በድርሰቶቹ ውስጥ ከሴትነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሃሳቦችን በማውጣት በገለጻ መልክ የሚያቀርብ ስለሆነ ነው፡፡

## 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት (የኤም.ኤ.ቲሲስ) በአራት ምዕራፎች የተደራጀ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ ሲሆን በሥሩም፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ የጥናቱ ወሰን እና ውስንነቶች እና የጥናቱ ሥነዘዴ የተሰኙ ክፍሎችን ይይዛል፡፡ ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝትን የሚይዝ ሲሆን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ተደራጅቷል፤ የመጀመሪያው ክፍል የንድፈ ሀሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ የቀረበበት ሲሆን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ በቅደም ተከተል በሁለተኛው እና በሶስተኛው ክፍሎች ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና ሲይዝ፣ ምዕራፍ አራት ደግሞ በጥናቱ የተደረሰበትን ውጤት በማጠቃለል አቅርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ

## 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ

### 2.1.1. የአንስታይ ሂስ ምንነት

አንስታይ ሂስ በተለያዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ሴቶች እንዴት ቀርበዋል የሚለውን የሚፈትሽ የሂስ አይነት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Tyson (1999) እንደገለጸችው አንስታይ ሂስ ሰፋ ባለ መልኩ ሲታይ ሥነጽሑፍ እና ሌሎች የባህል ዘርፎች የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነልቦናዊ ጭቆናዎችን መፍትሄ የመስጠት ሂደትን ወይም የሴቶችን ጭቆና የሚያባብሱ ሁኔታዎችን የሚመረምር የጥናት ዘርፍ መሆኑን ታብራራለች፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው አንስታይ የሥነጽሑፍ ሂስ በአንድ የሥነጽሑፍ ሥራ ውስጥ ሴቶች በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ መመርመር ነው፡፡ ይህም ማለት የወንዶችን የበላይነት መቃወም፣ የሴቶችን ጭቆና ማስቀረት እንዲሁም ዓባዊ ሥርዓት በሴቶች ላይ የሚያደረሠውን ተጽዕኖ መቀነስ እንደሆነ መገንዘብ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የአንስታይ ሂስ ዋና ዓላማ የተጨቆኑ ሴቶችን ከወንዶች እኩል በማሳተፍ ያላቸውን ክፍተት መቀነስ ወይም ማሻሻል ነው፡፡

እንደ Tyson (1999) ገለጻ ዓባዊ የሆነው የሥርዓተ ጾታ ሚናዎችን (Traditional gender roles) ስንመለከት ወንዶችን ጠንካራና ወሳኝ አድርጎ የማየት እና የመፈረጅ በተቃራኒው ደግሞ ሴቶችን ደካማ እና የተመደበውን የቤት ውስጥ ሥራ ብቻ የሚሰሩ አድርጎ የመቁጠር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሴቶች ለአመራር እና ለውሳኔ ሰጭነት ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እና በተጨማሪም በተመሳሳይ ሥራ እኩል የሆነ ክፍያ አያገኙም በማለት ትገልጻለች፡፡ እስከ አሁን ባለው የሥነጽሑፍ ዳሰሳ ሴቶች የወንዶች የበላይነት መዋቅር በባህላዊ እምነት እና አስተምህሮ ውጤት አምነው መቀበላቸው የሚያሳዩ ሲሆን ይህም ሴቶች የተጨቆኑና በተጽዕኖ ውስጥ እንደነበሩ የሥነጽሑፍ ታሪኮች ይመሰክራሉ፡፡ ማህበረሰቡ በሴቶች ላይ ያለውን የተሰሳተ ዕይታ እንዲያቆም መታገል የአንስታይ ሂስ አራማጆች ዋና አላማ ነው፡፡

Selamawit (2002) Ruthven (1984) ጠቅሳ አንስታይ ሂስ ብቸኛ እና የተሻለ የጥናት ዘዴ ነው ብሎ ማሰብ ተገቢ ሳይሆን በተግባር የማኅበረሰቡን አመለካከት መቀየር መቻል አለበት

በማለት ታስረዳለች። በተጨማሪም አንስታይ ሂስ በወሬ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ በተግባር ማህበረሰቡን ስለሴቶች ያላቸውን አስተሳሰብ መቀየረ እንዳለበት ነው። የአንስታይ ሒስ ተግባር መሆን ያለበት ሴቶችን በተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በማሳተፍ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ እና የዓባዊ ሥርዓት ተጽዕኖ ማስቀረት ነው። ምክንያቱም በተግባር የማይሳተፉ ከሆነ ከወረቀት የዘለለ ለውጥ ማምጣት ስለማይችል ነው። በአጠቃላይ በሴቶች ላይ ያለው አመለካከት በጥናት ብቻ የሚመለስ አይደለም። ሥር ነቀል ለውጥ መደረግ አለበት። ለውጥ ማምጣት የሚችለው ደግሞ ሴቶችን በቀጥታ ተሳታፊ ማድረግ ሲቻል ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች ጋር በተያያዘ Belsey, Catherine and Jane Moore (1997) እንደገለጹት ሁሉን አቀፍ የአንስታይ ጽንስ ሀሳብ ትግል እውን እንዲሆን ሴቶችን በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች ላይ ማሳተፍ ሲቻል ነው በማለት ይገልጻሉ። የተጠኑ ጥናቶችን ወደ ተግባር መቀየርና በማኅበረሰቡ ዘንድም የነበረውን የዓባዊ አስተሳሰብ በማስወገድ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል የሚያሳትፍ ሥርዓት መኖር አለበት። ህግ መውጣት ብቻ ሳይሆን ህጎች ተፈጻሚ በመሆን የማኅበረሰቡን አመለካከት በተግባር መቀየር ይኖርበታል።

እንደ Tyson (1999) ገለጻ ሴቶች በዓለም ላይ ያላቸው ዋጋ ላቅ ያለ መሆኑን ማጉላት ለነገ የማይባል ተግባር ነው። ይህ ማለት ማንኛውም ደራስያን በድርሰቶቻቸው ሴቶችን የሚወክሉበት አግባብ የአባዊ ሥርዓት አስተሳሰብን በማስወገድ በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚዊ ጉዳዮች ላይ ከወንዶች እኩል ደረጃ ማሳተፍ ይኖርባቸዋል በማለት ትገልጻለች።

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ደራስያን በሥነጽሑፍ ሥራዎቻቸው ሴቶችን የሚስሉበት አግባብ በፊት የነበረውን ኋላቀር አስተሳሰብ የሚያስቀር እና ሴቶችን በሁሉም ዘርፍ እኩል የሚታዩበትንና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ በሚያንጸባርቅ መልኩ ማቅረብ እንዳለባቸው ያስገነዝባል።

### 2.1.2. ሴቶችና ሥነጽሑፍ

በሴቶች እና በሥነጽሑፍ ዙሪያ ሁለት ሃሳቦች ይነሳሉ። የመጀመሪያው ስለሴት ጸሐፊያን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሴቶች በሥነጽሑፍ ውስጥ እንዴት ይወከላሉ ወይም ተስለዋል የሚሉት ናቸው። የሥነጽሑፍ ታሪክን በተመለከተ Sonia Choukri Bouziani (2015) እንደሚከተለው ታስረዳለች።

> *ምንም እንኳን በርካታ የሴት ጸሐፊዎችና መሪዎች ቢኖሩም ከነዚህ መካከል የግሪኳ ሴት ገጣሚ Sappho፣ ከአፍሪካ የግብጿ ንግስት Hatshepsut፣ የኢትዮጵያዋ ንግስተ ሳባ፣ የበርበራዋ ንግስት Kahina፣ የአልጀሪያ ንግስት Tin Hinan ሲሆኑ እነዚህ እንስቶች በሥነጽሑፍ ሥራዎቻቸው አልተበረታቱም ነበር። ከዚህ በተጨማሪም እንደ Alice Bradley Sheldon መሰል በብዕር ስም ይጽፉ የነበሩ ናቸው። በአሜሪካ በ1976 James Tiptree, Jr በሚል የብዕር ስም የተጻፈ* The Brontë *የሚል መጽሃፍ በሁለቱ እህትማማቾች* (Ellis,Acton, and Currer Bell) *በኋላ እውቅና ሲሰጣቸው በእውነተኛ ስማቸው መጻፍ የቻሉ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ* Mary Ann Evans (George Eliot) *እራሷን ግልጽ ያደረገችው Adam Bede የሚለውን (1856) የጻፈችውን መጽሕፍ እውቅና ካገኘች በኋላ ነው።*

ከላይ የተገለጹት እንስት ጸሐፊዎች ስኬታማ መሆናቸው የሚታወቅ ቢሆንም ሥራዎቻቸውን እንኳን በራሳቸው ስም ለማሳተም አለመቻላቸውን የሚያሳይ ነው። ይህ ሁኔታም ከጥንት ጀምሮ በሴቶች በርካታ ሥነጽሑፎች የተጻፉ ቢሆንም ሴቶቹ በወንዶች ላይ ጥገኛ መሆናቸውን ያሳያል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በሥነጽሑፍ ውስጥ እንዴት ተስለዋል የሚለውን ስንመለከት በዝቅተኛው መደብ ላይ የሚወከሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። በዓባዊ አስተሳሰብ ሴቶች በሥነ ጽሑፍ ሲወከሉ መጠነ ሰፊ የሆነ ተጽዕኖ ይደርስባቸዋል። ምንም እንኳን ከ1960ዎቹ የሴቶች እንቅስቃሴ በኋላ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱ ቢሆንም በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ያላቸው ውክልና ከወንዶች ያነሰ እንደሆነ ጥናቶች ያስረዳሉ በማለት Tyson (1999) ታስረዳለች።

በተጨማሪም Josephine (1989) እንደምታስረዳው የሥነጽሑፍ ትችት መቀየር ዋናው ምክንያት የዚያ ዘመን ድርሰቶች በወንዶች የበላይነት የተቃኙ መሆናቸው ነው። ስለዚህ የነበረውን የሥነጽሑፍ ዘይቤ ተቀይሮ ሴቶችን ያማከለ እና ከዚህ ቀደም ከነበረው ምልከታ የተለየ መሆን አለበት በማለት ያስረዳል። በቀደምት ጽሑፎች ላይ የሚታየው አጠቃላይ እይታ ለወንዶች ያዳላ ነበር። በመሆኑም ይህንን በማስወገድ የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ አንስታይ ሂስ ትኩረት ያደርጋል።

Brown and Karen (1978) እንደሚገልጹት የለውጥ መንገድ ክለሳ አዲስ ዕይታ የነበረውን ድርሰት በአዲስ መልክ መጠቀም የግድ ነው። ይህ ማለት በቀደሙ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የሴቶች እውቅናን የነፈገ ስለነበር የነሱን ጭቆና ለማስቀረት እንደገና የሴቶችን እኩልነት እና ተሳትፎ ያማከለ እንዲሆን የሥነጽሑፍ ሥራ በድጋሜ መታየት አለበት።

በቀደምት ሥራዎች ለሴቶች የሚሰጣቸው ውክልና ልጅ ወልዶ ከማሳደግ እና የቤት እመቤት ከመሆን የዘለለ አልነበረም፡፡ ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ውክልና ከመስጠት ይልቅ በሁሉም የሥራ መስኮች ከወንዶች እኩል ማሳተፍ ይኖርባታል፡፡ ይህን ሀሳብ በመደገፍም Selamawit (2002) Ruthven (1984) ጠቅሳ ሴቶች በሥነጽሑፍ ታሪክ አለመኖራቸው የወንድ የበላይነት ሥርዓት ማስረጃ እንደሆነ ታስረዳለች፡፡ የሴቶችን መድሎ ተከትሎ የሴቶች ሥራ ያተኮረው በምዕራባውያን የወንድና ሴትን ግንኙነት መሰረት ያደረገ እና የተዛቡ ታሪኮችን ማስተካከል ነበር፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ የሚያመለክተው በቀደምት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የሴቶች ውክልና ዝቅተኛ ደረጃ እንደነበረ ነው፡፡ ይህ ማለት የሥነጽሑፍ ሥራው ለወንዶች ያዳላ እንደ ነበረ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም አንስታይ ሂስ ይህን የተሳሳተ እሳቤ ማስተካከልና ሴቶችን በተለያየ የሥነጽሑፍ ዘረፍ በጠንካራ ገጸባህሪያትነት እንዲሳተፉ በማድረግ የተዛባውን አስተሳሰብ እንዲቀረፍ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ ሥነጽሑፍ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚደረሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳየት የሴቶችን ጭቆና እንዲቀንስ የራሱ የሆነ ፋይዳ አለው፡፡

Evans (1997) ከዚህ ጋር በተያያዘ እንደሚከተለው ትገልጻለች፡፡

> ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በ1970ዎቹ በአንስታይ ሂስ አቀንቃኞች የተደረሱ ጽሑፎችን ማንኛውም ሰው ማንበብ አለበት፡፡ ምክንያቱም በዓለም ላይ ያሉትን ማኅበራዊ ችግሮች ከስር መሰረታቸው ነቅሎ ለመጣል ስለሚያስችሉ ነው፡፡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሳይቀር የአባዊ አስተሳሰብ መንሰራፋት በሥነ ጽሑፉ የሴቶች ውክልና የሴቶችን ጀግንነት እውቅና የነፈገ ነው፡፡ ወንዶች ከሴቶች ጋር ሲነጻጸሩም ለሴቶች እድገት እንቅፋት ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ከ1970 በኂላ ሴቶች በሥነ ጽሑፍ የነበራቸው ሚና እያደገ መጥቷል፡፡

ከላይ ያሉት ሀሳቦችን ሲጠቃለሉ አንስታይ ሂስ አራማጆች በሥነጽሑፍ ውስጥ የሴቶችን እኩልነት ለማስጠበቅ ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ሂስ ከመጀመሩ በፊት ሴቶች ከወንዶች ያነሰ አቅም እንዳላቸው በማሰብ በተሻለ ሥራ ላይ አያሳትፏቸውም ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ባለንበት ደርጃ ሴቶች በሥነ ጽሑፍ ዘርፎች ማለትም በልቦለድ፣ በድራማ፣ በግጥም ሥራዎች ላይ በተለያየ መንገድ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ እየተሸሻለ እንደመጣ ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም የአንድ የሥነጽሑፍ ሥራ ደራሲ የማኅበረሰቡ አባል በመሆኑ የማህበረሰቡን አመለካከት ያንጸባርቃል፡፡

### 2.1.3. ዓባዊ ሥርዓት

ዓባዊ ሥርዓት በማኅበረሰቡ ዘንድ ሴቶችን የበታች አድርጎ ሲቆጥር የነበር የቆየ አመለካከት ሲሆን ይህም በማኅበረዊ፣ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ የወንዶችን የበላይነት ያረጋገጠ ነበር፡፡ ይህን በተመለከተ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001) እንደሚገልጸው ‹‹ዓባዊ ሥርዓት (patriarchy) የተባዕት የበላይነት አንዳንዴም ተጫኝነት እና ጨቋኝነት የሰፈነበት ማኅበራዊ ሥርዓት መጠሪያ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ውስጥ የማኅበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ቤተዘመዳዊ እና ባህላዊ ተቋማት የሚተዳደሩበት በወንዶች ይሆናል›› በማለት ይገልጻል፡፡

ከገለጻው የምንረዳው ዓባዊ ሥርዓት ወንዶችን የበላይና ጨቋኝ ሴቶችን ደግሞ የበታችና ተጨቋኝ አድርጎ የሚቆጥር ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሴቶች በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንዲሆን ጫናያደረገባቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

Keith and Bihan (1996) በበኩላቸው ዓባዊ ሥርዓት በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳዮች እንዲሁም በቋንቋ ውክልና ጭምር ወንዶችን የበላይ አድርጎ የቆየ አዕምሯዊና በተግባር ሲገለጽ የነበረ ሥርዓት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተየያዘ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም (1978፡) እንደገጸው

> ዓባዊ ሥርዓት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በቤተሰብ ኑሮ ረገድ የወንድ የበላይነት የሰፈነበት የጥንት ማኅበረሰብ ሥርዓት ነው፡፡ ወትሮ ሴቶች ተሰማርተውባቸው የነበሩትን ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም ከብት ዕርባታን፣ አሳ ማስገር፣ እርሻ፣ አደን ወዘተ… ወንዶች እየተረከቡ ሲሄዱ ሴቶች በማጀት ተወሰኑ፡፡ በአንድ በተደራጀ ማኅበረሰብ ውስጥ እና በግለሰብ ግንኙነት ውስጥ የወንድ ተቆጣጣሪ ሀይል አለ፡፡ ዘመናዊ የታሪክ ተመራማሪዎችና የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ዓባዊ ሥርዓትን ሲገልጹት ወንዶች የሀላፊነት ቦታዎችን እንዲያገኙ የበለጠ እድል አላቸው፡፡ የቤተሰብ መሪ፣ የማህበራዊ ቡድኖች መሪዎች፣ የሥራ ቦታ አለቃ እና የመንግስት መሪዎች በመሆን ትልልቅ ቦታዎችን ስልጣን ይይዛሉ በማለት ይገልጻል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው ዓባዊ ሥርዓት ሴት ወደማጀት ወንድ ወደችሎት የሚለውን የአገራችን ብሂል የተከተለ ሲሆን የወንዶችን የሃይል ሚዛን ወይም የበላይነት ለማስቀጠል እንደ መሳሪያ የሚጠቀሙበት ስልታቸው ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት የሴቶች ድርሻ በወንዶች የተገደበ ነው፡፡ በሴቷ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በወንዱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የሥራ

ድርሻ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ በዚህ የዓባዊ ሥርዓት ወንዶች የተለያዩ ሥልጣኖችን በእነሱ ቁጥጥር ሥር በማዋል የበላይነቱን ሲወስዱ ሴቶችን በቤት ውስጥ ሥራዎች ላይ እንዲወሰኑ አድርጓቸዋል፡፡

Gerdalerners (1986) ዓባዊ ሥርዓት ወንዶችን የበላይ ስለሚያደርግ ለአንድ ማኅበረሰብ እድገት ጥሩ አለመሆኑን ታስረዳለች፡፡ ምክንያቱም ሴቶች በማኅበረሰቡ ውሰጥ ያላቸው ሚና የማይተካ ስለሆነ ነው፡፡ ዓባዊ ሥርዓት በተለያዩ ዘርፎች በመግባት በሴቶች ላይ አካላዊና ሥነልቦናዊ ተጽዕኖ ሲያደርስ የቆየ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የሚገባባቸው ዘርፎች በርካታ ቢሆኑም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም መደብ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህንም በተናጠል እንደሚከተለው እንመልከታቸው፤

### 2.1.3.1. ሴቶች እና ኢኮኖሚ

ያለፉት ዘመናት በወንዶች ገዥነት እና በሴቶች ተገዥነት ታሪክ የተገነባ ነው፡፡ Lynn (1976) እንደገለጸው አባዊ ሥርዓት ዋና ማጠንጠኛው በወንዶች የበላይነትና እና በሴቶች የበታችነት ላይ የተመሰረተ እንደነበረ የሚያመላክት ሲሆን ወንዶች የኢኮኖሚውን ስልጣን ለዘመናት በበላይነት ይዘውት ኖረዋል፡፡ ሴቶች በከፍተኛ የኢኮኖሚ ደርጃ ላይ ሳይሆን የሚወከሉት ቤት ውስጥ ያሉ ሥራዎችን በማክናወን እና ልጆችን በመንከባከብ ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ሴቶች እንደወንዶች በተለያዩ ዘረፎች የማይሰሩና የችሎታ ማነስ ኑሮባቸው ሳይሆን ዓባዊ ሥርዓቱ ተጽዕኖ ስላሳደረባቸው ነው በማለት ያስረዳል፡፡

ሴትነት እና ልማት ስናስብ ቀድመው የሚመጡት ጉዳዮች የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚሉ ሃሳቦች ናቸው፡፡ በ1980 የተጀመረው የሴቶች የልማት እንቅስቃሴ ቀደም ሲል ሴቶች በልማት ዘርፍ ከወንዶች ጋር የታዩ ልዩነቶችን አጉልቶ በማውጣት የተሻለ እኩልነትን ለማስፈን ሲባል የተካሄደ ነው፡፡ በእኩል ደረጃ ለሴቶች እና ለወንዶች የተመቻቼ ሁኔታ ባለመኖሩ ፍትሃዊ ያልሆነ ግንኙነት እንዲኖር አድርጓል፡፡ ከዚህ ቀደም ባሉት ሥነጽሑፎች ሴቶችና ወንዶች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተለያይተው ይሰለፋሉ፡፡ ዓባዊ ሥርዓት ለሴቶች የሚሰጣቸው አመለካከት ዝቅ ያለ በመሆኑ የሚመደቡበት የሥራ ደርጃም ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያየዘ Carol and Mark (1976) እንደሚያስረዱት የዓባዊ ሥርዓቱ ሴቶችን በኢኮኖሚ እንዳይሳተፉ አድርጓቸው ቆይቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ስለሴቶች በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው አስተሳሰብ ተጽዕኖ ፈጥሮ መቆየቱ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ዓባዊ ሥርዓቱ ሴቶች ከወንዶች እኩል በኢኮኖሚው ዘርፍ እንዳይሳተፉና ራሳቸውን እንዳይመሩ አድርጓቸው እንደቆየ ያመለክታል፡፡ ይህም የሆነው ሴቶች በተፈጥሮ ደካማ ሆነው ሳይሆን የማህበረሰቡ የተዛባ ግንዛቤ በተለያዩ የሥራ መስኮች እንዳይሳተፉ አድርጓቸው የቆየ መሆኑን ነው፡፡

Cheryll and Karen (1978) እንደሚያብራሩት በዓባዊ ሥርዓት ውስጥ ሴት የምትለካው ለባሏ በአላት ታማኝነት፣ ፍቅር፣ በባሏ ስኬት፣ ልጅ በመውለድ እና የቤት ውስጥ ስራዎችን በማከናወን ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከገለጻው መረዳት እንደሚቻለው የሴቶች ብቃት የሚለካው በባሏ ስኬታማነትና በባሏ ላይ በምትጨምራቸው እሴቶች እንጅ በራሷ ብቃት በምታስመዘግባቸው ውጤቶች የምትመዘን አለመሆኑን ነው፡፡

Carol and Mark (1976) ገለጻ በ19ኛው እና በ18ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ስለሴቶች የነበረው ግንዛቤ ሴቶች ከቤት ወጥተው ሥራ የመስራት አቅማቸው አነስተኛ መሆኑንና ትላልቅ ውሳኔዎችን የመወሰን እጥረት እንዳለባቸው ተደርጎ ይታይ ነበረ ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ ይህ ሃሳብ የሚያስረዳው ሴቶች ባለፉት ዘመናት በተለያዩ ዘርፎች ተጨቁነው እንደነበር አመላካች ነው፡፡ Bengsten (1977) የተባለችው የእንስት ንድፍ ሀሳብ አቀንቃኝ ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ ያላቸውን ሚና እንደሚከተለው ትገልጻለች፡፡

> ሴቶች በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ በጥቃቅን ሥራዎች የሚሳተፉ ቡድኖች ናቸው፡፡ ትላልቅ ሥራዎችን የመምራት አቅም የላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ የመሳተፍ እድሉን ተነፍጓቸው ቆይቷል፡፡ በሥነጽሑፎችም ይሁን በሚነገሩ ታሪኮች ሴቶች የመምራት አቅም የላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ በትላልቅ የኢኮኖሚ ተቋማት ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ እንደሚያስረዳው በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ ሴቶች በዝቅተኛ ሥራዎች እንዲሳተፉ የሚያደረግ ሲሆን ላቅ ባሉ የሥራ መስኮችም አቅማቸው ደካማ ነው በሚል እድል እንደማይሰጣቸውና ይህም በሥነጽሑፎች ጭምር ይንጸባረቅ እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.3.2. ሴቶችና እና ማህበራዊ ጉዳዮች

በአብዛኛው የማህበረሰባችን ክፍል ወንዶችን የቤተሰብ ሃላፊ፣ ሴቶችን ደግሞ ጥገኛ እና ህጻናትን አሳዳጊ ብቻ አድርጎ ማሰብና ይህንኑ ሚና እንዲጫወቱ መገፋፋትና ማስገደድ በማህበራዊ መስክ የተለመደ ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ Bellesy and Moore (1997) እንደገለጹት፡-

> ሴቶች በማህበራዊ ንቅናቂያቸው ምክንያታዊ አስተሳሰቦችን በመያዝ የወንዶችን የበላይነት በመቃወም ጾታዊ መድሎ እንዲለወጥ በቁርጠኝነት ትግል አድርገዋል፡፡ በማህበራዊ የሴቶች የስልጣን ክፍፍል ጾታን መሰረት ያደረገ ሳይሆን የግለሰባዊ ችሎታን ያማከለ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ የአንስታይ ጽንስ ሀሳብ ማህበረሰብን፣ ተቋማትን፣ ኢኮኖሚን እና የስልጣን ክፍፍልን መዳሰስ ይኖርበታል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሴቶች በማህበረሰቡ ዘንድ የሚደርስባቸውን ጫና ለመታገል ምክንያታዊ የሆኑ ሃሳቦችን በማንገብ በወንዶች የሚደርስባቸውን ጭቆና እንዲሁም በሚደረጉ የስልጣን ክፍፍሎችም ችሎታንና ጾታን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ሲታገሉ የቆዩ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ሥርዓተ ጾታን በተመለከተ ስነህይወታዊ ባህርያትን በመያዝ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለና የሚኖር፣ ሊለወጥ የማይችል ማንነት ነው፡፡ ነገር ግን ሰዎች በማህበራዊ ግንኙነትን፣ በኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችና በፖለቲካዊ ተሳትፎ ልዩነትን መፍጠሪያ ያደርጉታል፡፡ የጋብቻ ስነ ስርዓትን በመውሰድ ለማየት ቢሞከር እንኳን በሁለቱ ጾታዎች ልዩነት አለ፡፡

ይህን በተመለከተ ብርሃን (2009) በጥናቱ እንዳመለከተው ‹‹ለሴትና ለወንድ የሥርዓተ ጾታ ልዩነት መፈጠር አንዱ ምክንያት በዓለም ላይ ያለው ልማዳዊው የሆነው የጋብቻ ሥርዓት ነው፡፡ ይህም ጋብቻ ሲፈጸም ወንዱ ሴቷን ወደ ራሱ ቤተሰብ አምጥቶ ያቀላቅላል እንጅ ራሱ ሄዶ ከሴቷ ቤተሰቦች ዘንድ አይገባም›› የሚል ነው፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ ወንዶች ሀይላቸውን ለማሳረፍ እና ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ከተጠቀሙባቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ ሴቶችን መለየት ነው፡፡ ይሄ በጋብቻ ጊዜ የሚፈጠረውን ከቤተሰብ መለየት ይመለከታል፡፡ በዚህም የተነሳ ሴቷ የማታውቀው ቤተሰብ ውስጥ ስለምትገባ ዝም የማለትና ጎልታ በማትታይበት የቤት ውስጥ ሥራዎች ላይ እንድትጠመድ ተደረጋለች፡፡ ይህም በሂደት የዝቅተኝነት መንፈስ ያሳድርባትና ከወንድ እኩል

እንዳትሆን ሥነልቡናዊ ጫና ይደርስባታል። እነዚህም ሁኔታዎች በሂደት የሴቷንና የወንዱን የኃይል ሚዛን ሊያዛቡ እንደሚችሉ ይገመታል። ምክንያቱም ሴቷ የማታውቀው ቤተሰብ ውስጥ ሄዳ ስለምትቀላቀልና የባይተዋርነት ስሜት ስለሚያመጣባት ታዛዥነትን ትመርጣለች። የእርቅ ስርዓትም ብንመለከት ሴቶች ከወንዶቹ ዝቅ ተደርገውና ተገልለው የሚተገበርበት ሂደት እንዳለ ያሳያል።

ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ብርሀን (2009) ተመስገን (2004) ጠቅሶ እንደገለጸው ‹‹በዶኮ ጋሞ የእርቅ ሥርዓት ጊዜ ሴቶች አይታደሙም። ጉዳዩ የእነሱ ቢሆንም እንኳ በርቀት ተቀምጠው ሲጠየቁ ይናገራሉ፤ ወይም በስማ በለው ሃሳባቸው ይነገርላቸዋል እንጅ እነርሱ ቀርበው አይናገሩም።›› ይህ ሃሳብ እንደሚያመለክተው የሴቶችን ሚና ዝቅ በማድረግ ወንዶችን እንደ አስተዋይ፣ ጠንካራ፣ ተከላካይና ወሳኝ እንዲሁም ሴቶችን እንደ ስሜታዊ ደካማ፣ ድጋፍ ፈላጊዎችና ተሸናፊዎች አድርጎ ማየቱን ነው። ለዚህም ማሳያው ሴቶችን በተለያዩ የእርቅ ስነስርዓት ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ አለመሆናቸው ነው።

Fischer, Patricia and Vianen (2004) በጥናታቸው እንዳስቀመጡት፡-

> ሴቶች ያላቸውን ስሜት በመከፋት፣ በፍርሃት፣ በሃፍረት እና በጥፋተኝነት መንፈስ ሲገለጽ የወንዱ ግን በቁጣና በሌሎች መሰል ስሜቶች ይንጸባረቃል። ይህ ስሜት የተፈጠረው ማህበረሰቡ በሴቶች ላይ በሚያደርስባቸው የተሳሳተ አመለካከት ነው። ስለዚህ እነዚህንና መሰል ተግባራት በማስወገድ የሴቶችን ተሳትፎ ማበረታታት ከማንኛውም ሴቶችም ሆነ ወንዶች የሚጠበቅ ተግባር ነው በማለት ይገልጹታል።

Phillips (1993) እንደአብራራችው ማህበራዊ አገልግሎት ሰጭዎች በስርዓተ ጾታ ቁርጠኝነት ክንውን ሴቶችን በእናትነት ልጆቻቸውን የሚንከባከቡና ለወንዶች የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚሰጡ ብቻ አድርጎ መመልከት መፍትሄ ሊፈለግለት ይገባል። የቤተሰብን ችግሮች በሴቶች ላይ ብቻ መጣልና ቤተሰብ የመመገቡን ሚና ለሴቶች፤ ወንዶችን ደግሞ አይነተኛ የገንዘብ አቅራቢዎች አድርጎ መመልከት ተገቢነት የለውም።

እንደ Bilote (1975) አገላለጽ የሴቶች ንቅናቄ አራማጆች ጥብቅ አቋም የማህበራዊ ሰራተኞች የጾታ ልዩነት በወንዶችና ሴቶች ከዚያም አልፎ በሴቶችና ሴቶች የተወሰነ አይደለም። በተቋማዊና ባህላዊ አውድ ስርዓተ ጾታን በጨለምተኝነት የማየት አዝማሚያ ይስተዋላል። ከዚህም ባለፈ ሴቶች እራሳቸው በዘርም ሆነ በመደብ ሌሎች ሴቶችን ሊጨቁኑ ይችላሉ። ለአብነትም የነጭ መካከለኛ መደብ ሴት የጥቁር መካከለኛ መደብ ሴት ጋር በማህበራዊ

አገልግሎት አሰጣጥ አጋጣሚ ሲገናኙ ጥቁሯን እንደ ጽዳት ሰራተኛ ግምት ከተሰጣት ይህ ሁኔታ የዘር ልዩነትን ያሳያል፡፡

Groum Wood and plastron 1993፣ Demnile (1997) እንደሚገልጹት የስርዓተ ጾታ ግንኙነት የሰመረ ቦታ ሊይዝ የሚችለው ሴቶች እንደወንዶች በአስተዳደር ቦታዎች ላይ ሲቀመጡ ነው፡፡ ነገር ግን ሴቶች በስራ አስኪያጅነት ስልጣን ላይ ቢቀመጡም ማዕረጋቸው ዋጋ ቢስ ነው፡፡ ይህም ከወንድ የስራ ጓደኞቻቸው ጋር ሲገኙ ሴቶቹን ብቁ አለመሆናቸውን ለማሳየት የተለያዩ ተጽዕኖዎችን ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡ ሴት ስራ አስኪያጆች ከወንዶች አቻዎቻቸው ጋር ከተገቢው በላይ የሆነ ግንኙነት ሊያሣዩ ይችላሉ፡፡ በዚህም የድጋፍ መረብ ሊዘረጉ ይችላሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡

Demnile (1989) እንደገለጹት የሴቶች ንቅናቄ ዓላማ ሴቶችን ከአስቸጋሪ ህይዎት በማላቀቅ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን የበታችነት ደረጃ ማስቀረት ነው፡፡ ይህ ማለት የሴቶች ንቅናቄ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪዎች የሴቶችን ማህበራዊ ደረጃና ሚና መነሻ በመለየት በኩል እንደሴትነታቸው ቀዳሚ ናቸው፡፡ የሴቶች ማህበራዊ አገልግሎት በመፍጠር ደረጃ ተራማጅ ሴቶችን በሴቶች ንቅናቄ ዙሪያ ማንቃት ችለዋል፡ ይህም ወደራሳቸው ልዩ ንድፈ ሃሳብና ትግበራ ለመግባት አስችሏል፡፡ በዚህም የተነቃቃ ግንኙነትና ማህበራዊ አገልግሎት ለነጻ ትምህርት እድል፣ ምርምርና ትግበራ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የሴቶች ንቅናቄ የማህበራዊ አገልግሎት አንድ ዘርፍ ሲሆን ይህም በሴቶችና በህብረተሰቡ መካከል ያለ ግንኙነትን አስመልክቶ የራሱ ትንታኔ ያለውና አቅጣጫ የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሴቶችን አስቸጋሪ ህይዎት በንድፈሃሳብ ደረጃ ያነገበ ሲሆን ሴቶች በማህበረሰቡ ዙሪያ የሚሰጣቸውን ቦታ የሰመረና ወደእኩልነት የሚያመጣ ነው፡፡ የሴቶችን ፍላጎት በማሟላት ረገድና በህይዎታቸው የሚገጥሟቸውን ውጣ ውረዶች በማቃለል የሴቶችን ንቅናቄ ማህበራዊ አገልግሎት በርካታ ተግባራትን የሚያከናውን እንደሆነ ያሳያል፡፡

### 2.1.3.3. መደብ

መደብ የሚለው ቃል ተመሳሳይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ የትምህርት ሁኔታና በአጠቃላይም ተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ይመለከታል፤ በማለት http://udel.edu/~cmarks/What%20is%20social%20class.htm. የተሰኘ ድረገጽ

ያስረዳል። ከሃሳቡ መረዳት የሚቻለው መደብ ተመሳሳይ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ በአጠቃላይም በሰው ልጆች አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ተመሳሳይ ማንነት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚመለከት መሆኑን ነው።

Wikipedia የተሰኘ ድረገጽ በበኩሉ መደብን ለመወሰን የሚያስችሉ ጉዳዩች የተፈጥሮ ሀብቶች፣ ሃይል፣ ስልጣን፣ ገንዘብ፣ መሬት፣ ደመወዝ፣ መሰረተ ልማት፣ ተጽዕኖ መፍጠር መቻል፣ ለራሳችን ያለን ክብር፣ ለሌሎች የሚሰጥ ክብር፣ እውቀት፣ ውበት፣ ሙያ፣ ታዋቂነት፣ ትምህርት፣ ዘር ወዘተ... መደብን የሚወስኑ ጉዳዮች ናቸው ሲል ይገልጻል።

በተመሳሳይም Banks (1999) በአብዛኛው መደብን ለመወሰን ከሚያስችሉ ጉዳዮች ውስጥ የገቢ መጠን፣ ትምህርት፣ ስራ፣ የኑሮ ደረጃና እሴቶች /values/ ናቸው። ነገር ግን የትኛው የበለጠ ይወስነዋል በሚለው ላይ የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ዘንድ ስምምነት የለም በማለት (Warner 1960) ጠቅሶ ያስረዳል።

ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች የሚያስረዱት በሰው ልጆች ላይ ተጽኖ የሚያሳድሩና ልዩነትን የሚፈጥሩ የተለያዩ ነገሮች እንዳሉና እነሱም ግለሰብን ከግለሰብ ማህበረሰብን ከማህበረሰብ ነጥለው ለማየት የሚያስችሉ መሆናቸውን ነው። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ተፈጥሮ ሀብቶች፣ ትምህርት፣ ሙያ፣ የገቢ መጠንና የኑሮ ደረጃ የሚሉት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ነው። የመደብ ልዩነት ከሚጠናባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የማርክሲዝም ንድፈሃሳብ ነው። የማርክሲዝም ንድፈ ሀሳብ ሴቶችን ከመደብ፣ ከኢኮኖሚና ከአባዊ ስርዓት አንጻር የሚመለከት ወይም ትንታኔ የሚሰጥ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም Madsen (2000) እንደገለጸችው:-

> ማርክሳዊ ንድፈ ሀሳብ ሴትነትን ከካፒታሊዝም፣ ከዓባዊ ሥርዓት እንዲሁም ከመደብና ጾታዊ ጭቆና ከሚሉ መሰረታዊ የቅራኔ ሃሳቦች የተዋቀረ ነው። ማርክሳዊ ንድፈ ሀሳብ በመደባዊ ጥናትና በጾታዊ ትንተና ውህደት የተፈጠረ ነው። ካፒታሊዝም የሚመለከተው የጾታንና ኢኮኖሚያዊ አለመጣጣምን ሲሆን አባዊ የሆነው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ደግሞ ለሴቶች ጭቆና ምንጭ ነው ተብሎ ይታመናል። አባዊ የሆነው የወንዶችን የበላይነት ሥርዓት ወንዶች የሁሉም ነገር አራጊና ፈጣሪ ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ ተቀባይ እና እንደየበታች ተደርገው የሚቆጠሩ ናቸው። የቆየው አመለካከት (እይታ) የሁሉም ሴቶች ኢኮኖሚ በወንዶች ላይ ጥገኛ የሆነና በወንዶች የሚመራ ነው:: ይህም የመደብ ልዩነት እንዲፈጠር አድርጓል በማለት ታስረዳለች።

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ የሴቶችን ንቅናቄ ከመደብ ትግልና ከሥርዓተ ጾታ ትንታኔ ጋር የሚያዛምድ መሆኑን ነው። በሴቶች ላይ የሚደረግ የጉልበት

ብዝበዛ ሁሉንም ሴቶች የሚመለከት ሲሆን አባዊ ርዕዮተ ዓለም ወንዶች በሴቶች ላይ የበላይነት እንዲጎናጸፉ እንደሚፈቅድላቸው ያስገነዝባል፡፡

Madsen (2000) እንደምታስረዳው ምንም እንኳን በመደብ የተከፋፈለ ማህበረሰብ የሴቶች ጭቆና መሰረት ያደረገ ቢመስልም ውጤቱ ግን አባዊ ሥርዓት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ግለሰባዊና ባህላዊ ማንነቶች እንደ ርዕዮተ ዓለም ውጤት ተደርገው ይታያሉ፡፡ የሴቶች ንቅናቄ አራማጆች ከካፒታሊዝም ሥርዓተ ማህበር ጋር ቅራኔ ውስጥ የሚገቡት የሴቶችን አቅም ዝቅ አድርጎ በማየቱ ነው፡፡ ማርክሳዊ የሴቶች ንቅናቄ አቀንቃኞች ከማህበራዊ ሥርዓት አቀንቃኞች ጋር ልዩነት የሚፈጥሩት በሴቶችና በወንዶች መካከል የሚኖርን መሰረታዊ ክፍፍል የሚወስነው የመደብ ልዩነት ነው? ወይንስ ሥርዓተ ጾታ ነው? በሚለው ሃሳብ ላይ ነው፡፡

ማርክሳዊ የሴቶች ንቅናቄ አራማጆች የሥርዓተ ጾታ ልዩነት በነባራዊ የማርክሳዊ ትንታኔ ከተሰጠው የመደብ ክፍፍል ሚናን በመተካት ሥርዓተ ጾታ ላይ የሚያተኩር ትንታኔን በአይነተኛ ጭብጥነት ያነሳሉ፡፡

Barrett (1980) ስትገልጽ ማርክሳዊ የሴቶች ንቅናቄ በስርዓተ ጾታ ከተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት የቤት ውስጥ ተግባራት፣ የቤት ውስጥ አስተዳደርና የመሳሰሉት በስልት ምርት ለውጥ ላይ በብዝበዛና በባለቤትነት ላይ እንደሚያተኩር ጽፋለች፡፡ በማስቀጠልም የማርክሲስት የሴቶች ንቅናቄ አተያይ የዓባዊነት ጽንሰ ሀሳብን ከሥነህይወታዊ መሰረትና የሀይል ግንኙነት ጋር ሳይሆን ከተገቢ የሴቶች ጭቆና አኳያ ይተነትናል በማለት ትገልጻለች፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው የሴቶች ንቅናቄ አራማጆች እንደሚያስገነዝቡት ሴቶች ምንጊዜም በዓባዊ ሥርዓት አስተዳደር በደል የደረሰባቸው እና ይህ ደግሞ በካፒታሊዝም ወቅት የበለጠ ጥልቀት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ሴቶች ሴት በመሆናቸው ብቻ በተጠናከረ መልኩ በመደባቸው ይጨቆናሉ፡፡ በሥርዓተ ጾታ የሚደርስባቸው ጭቆና በሌላው ከሚደርሰው በተለየ የከፋ እንደሆነ Barrett (1980) ታስረዳለች፡፡ ምንም እንኳን ይህ ጽንስ ሀሳብ ህይወትን ከቁሳዊ ሁኔታ ጋር አዛምደው ማየቱ ጠቃሚ ቢሆንም  ርዕዮተ ዓለም ብቻውን በካፒታሊዝም ሥርዓት ያለውን የሴቶች ጭቆና መግለጽ አይችልም፡፡ ኢኮኖሚያዊ ሂደቶች ርእዮተ ዓለምን ወሳኝ የሚያደርጉት  ለሴቶች ጭቆና የተለየ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ነው፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

በዚህ ንዑስ ክፍል አጥኚው ከሚያጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መልኩ የሚገናኙ ጥናቶች አንድነትና ልዩነት የሚዳሰስበት ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም እስካሁን በተደረገው ዳሰሳ መሰርት ከጥናቱ ጋረ ተመሳሳያነት ያለው በአማርኛ ቋንቋ የተጠና የአጋረደች ጀማነህ ‹‹*ሴትነትና እናትነት* በፀሐይ መላኩ ልቦለዶች የሚለውን ጥናት ብቻ ያገኘሁ ሲሆን በተዘዋዋሪ መልኩም ከዚህ ጥናት ጋር አብረው የሚሄዱ ጥናቶች አልጠፉም፡፡ ከእነዚህ መካከልም ብርሃን አሰፋ (2009) "በተረቶች ውስጥ የታዩ የስርአተ ጾታና የስልጣን ኢፍትሀዊነት" የሚል የፒ.ኤች.ዲ ጥናት፣ እስክንድር ሀይሉ (2008) "የሴቶች ሚናና መስዋትነት በፖለቲካዊ ተውኔቶችና ፊልሞች ውስጥ" የኤም.ኤ ጥናት እንዲሁም አብርሃም አለሙ (2000) "ቃላዊ ተረኮችን እንደመሳሪያ በመጠቀም የሚከናወን የጅማ ኦሮሞ የሴቶች ተጽኖ" በሚል ለኤም.ኤ ዲግሪ የተሰሩ ጥናቶች የተዳሰሱ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱበትና የሚለያዩበት ነጥብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተመሳሳይነት ያለው የመጀመሪያው ጥናት የአጋረደች ጀማነህ (…) ‹‹*ሴትነትና እናትነት*›› በፀሐይ መላኩ ልቦለዶች የሚለው ነው፡፡ የአጋረደች ጥናት አላማ በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች በምን መልኩ እንደቀረቡ መተንተን ሲሆን ሰነድ ፍተሻን ተጠቅማ መረጃ በመሰብሰብ በትንተናዋም በደራሲዋ ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ሴት ገጸባህሪያት ሀይል አጠው በወንዶች የበላይነት ሲመራ አሳይታለች፡፡ *በቋሳ*፣ በ*አንጉዝ* እና *በቢስ ራሔል* ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ሴት ገጸባህሪያት በአስተሳሰብና በኢኮኖሚ የወንዶች ጥገኛ መሆናቸው ሲሆን የመጨረሻ ግባቸውም አግብቶ ልጅ በመውለድ ልጆችን የመንከባከብ ደረጃ ላይ መድረስ መሆኑን ከልቦለዶቹ በማሳያነት አቅርባለች፡፡

የአጋረደች ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ሴትነትን በርዕሰ ጉዳይነት በማንሳት ማጥናቷ የሚያዛምደው ሲሆን በአንድ ሰው ስራ ላይ ማጥናቷ፣ የልቦለዶቹ መለየት፣ ይዛቸው በተነሳቻቸው አላማዎችና የትኩረት ነጥቦችና በጊዜ የሚለያዩ ናቸው፡፡

ሌላው ብርሃን አሰፋ (2009) "በተረቶች ውስጥ የታዩ የስርአተ ጾታና የስልጣን ኢፍትሀዊነት" በሚል በደቡብ ወሎ ዞን 3 ወረዳዎች (ተሁለደሬ፣ ኩታበር፣ ቦረና) የተሰራ ሲሆን የጥናቱ አላማ ወንዶችና ሴቶች በተረቶች ውስጥ ምን ዓይነት ገጽታ እንደተሰጣቸው፣ ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸውን የሃብትም ይሁን የሥልጣን የበላይነት በተረቶች ለማስቀጠል የተቀሙባቸው ሥልቶች እና የሴቶች ብርታት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተወከሉባቸው ተረቶች ምን

እንደሚመስሉ መፈተሽ ሲሆን አጥኚው ለጥናቱ የተጠቀመባቸውን መረጃዎች ከመስክ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በተተኳሪ እንዲሁም ከሰነዶች በጥልቅ ንባብ ሰብስቦ ያጠና ሲሆን በውጤቱም ሥርዓተ ጾታዊ አድልዎ ሰፊ የባህል መሰረት እንዳለው፣ ይህም በተረቶች ውስጥ ተሰናስሎ እንደቀጠለ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

የብርሀን አሰፋ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ሴትነትን በርዕሰ ጉዳይነት በማንሳት ማጥናቱ የሚያዛምደው ሲሆን ይዞት በተነሳው አላማና የትኩረት ቦታ፣ በተረቶች ላይ መጠናቱ፣ በአጠናን ዘዴው፣ በተሰራብት ጊዜ የሚለያዩባቸው ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪም ብርሃን ባህሉን መሰረት በማድረግ ተረቶችን ያጠና ሲሆን ይኽ ጥናት ግን ልቦለዶቹ ውስጥ ባሉት ጭብጦች ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፡፡

ሌላው ጥናት እስክንድር ሀይሉ (2008) "የሴቶች ሚናና መስዋትነት በፖለቲካዊ ተውኔቶችና ፊልሞች ውስጥ" በሚል ርዕስ ሁለት ፊልሞችን በመውሰድ ከአንስታዊ ንድፈ ሀሳብ አኳያ ንጽጽራዊ ትንተና ያቀረበ ሲሆን መረጃዎችንም ምልከታና ቃለ መጠይቅን በመጠቀም ሰብስቧል፡፡ በትንተናውም ወንድ ገጸባህሪያት የበላይ፣ ሴት ገጸባህሪያት ደግሞ የበታች ሆነው እንደተሳሉና ሴቶች የተገዥነት ወንዶች ደግሞ የገዥነት ሚናን በመላበስ እንደቀረቡ አሳይቷል፡፡ የእስክንድር ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ሴቶች ላይ ትኩረቱን በማድረግ መጠናቱ የሚያመሳስለው ሲሆን በእንግሊዘኛ ቋንቋ መጠናቱ፣ በተውኔቶችና ፊልሞች ላይ መጠናቱ፣ ይዞት በተነሳው አላማና በትኩረት ነጥቦቹ፣ በአጠናን ዘዴውና በተሰራብት ጊዜ የሚለያዩባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች በተጨማሪ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው ጥናት የአብርሃም አለሙ (2000) "ቃላዊ ተረኮችን እንደመሳሪያ በመጠቀም የሚከናወን የጅማ ኦሮሞ የሴቶች ተጽኖ" የሚለው ጥናት ሲሆን መረጃዎችንም ቃለ መጠይቅን በመጠቀም ሰብስቧል፡፡ በትንተናውም ወንዶች የበላይ ሴቶች ደግሞ የበታች ሆነው እንደቀረቡ አሳይቷል፡፡ የአብርሃም ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ሴቶች ላይ ትኩረቱን በማድረግ መጠናቱ የሚያመሳስለው ሲሆን በእንግሊዘኛ ቋንቋ መጠናቱ፣ ቃላዊ ተረኮች ላይ መጠናቱ፣ ይዞት በተነሳው አላማና በትኩረት ነጥቦቹ፣ በአጠናን ዘዴውና በተሰራብት ጊዜ የሚለያዩባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አብርሃም ቃላዊ ተረኮች ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በረጅም ልቦለዶች ላይ ትኩረት የሚያደረግ መሆኑ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ሁሉም ጥናቶች ሴትነት ላይ ትኩረታቸውን በማድረግ መሰረታቸው የሚያመሳስላቸው ቢሆንም ከዚህ ጥናት ጋር ግን ከተጠኑበት ቋንቋ፣ ከሚያነሱት ጭብጥ

ወይም የትኩረት ነጥብ፣ በአጠናን ዘዴያቸው እንዲሁም ሌሎቹ በቃላዊ ስነጽሁፎችና ፊልሞች ላይ ያተኮሩ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ረጅም ልቦለዶች ላይ መሰራቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት:- ትንተና

## 3.1. የልቦለዶቹ አጽመ ታሪክ

*ምዕራባዊት* በ(2004 ዓ.ም) በአሰፋ በቀለ የተጻፈ ሲሆን በረጅም ልቦለዱ ውስጥ ዋና ገጸባህሪ የሆነችው ምዕራባዊት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር የጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ናት። ምዕራባዊት በስራዋ ታታሪ በአስተሳሰቧ የተሻለችና ሰውን መርዳት የሚያስደስታት በጎ ስነምግባርን የተላበሰች ሴት ናት። ምዕራባዊት አካሉ ልሳነወርቅ የተሰኘን ሰው አፍቅራ በራሷ ቤት ጠርታ አግባኝ ብላ በመጠየቅ ያገባችው ሲሆን ፍቅራቸው ግን ገና በጅምሩ ሊቀጭ ችሏል። ይህ የሆነበት ምክንያትም አካሉ ከዚህ በፊት አግብቶ አራት ልጆች የወለደና በሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ ምክንያት ትዳሩ ተበትኖ ልጆቹን እንኳ እንዳያይ በመከልከሉ ይስራበት የነበረውን አዲስ አበባን በመልቀቅ ሸሽቶ ወደጋምቤላ የሄደና አዲስ የፍቅር ሂዎቱን በጀምርበት ሰዓት ግን ባልተጠበቅ ሁኔታ ከአራት ዓመት በኋላ ከፈታት ሚስቱና ከልጆቹ ይቅርታን የሚጠይቅ በሀዘን የተሞላ ደብዳቤ በምዕራባዊት እጅ በመግባቱ ነው። ምዕራባዊት ምንም እንኳ አካሉን የምታፈቅረው ብትሆንም የቀደሞ ሚስቱ ለቅሶና የልጆቹ ናፍቆት ሁኔታ ስላሳዘናትና ስላስጨነቃት አካሉ ከእሷ ይልቅ ለባለቤቱና ለልጆቹ እንደሚያስፈልግ በማመን ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ወስናለች። በውሳኔዋም ጽንስ ከማስወረድ ጀምሮ ያላትን ሃብትና ንብረት በመሸጥ፣ እስር ቤት በመግባት ስቃይና እንግልትን በማስተናገድ በርካታ መስዋዕተነቶችን ከፍላለች። በውጤቱም የተለያዩ የማስታረቂያ ስልቶችን ተጠቅማ የተበተነ ትዳሩን ስትመልስለትና በዚህም ከተለያዩ አካላት ምስጋናና ምርቃትን ተቀብላለች። በመጨረሻም ‹‹ትኩረት ለቤተሰብ የእርዳታና የምክር አገልግሎት ድርጅት›› በሚል ስም ለተቋቋመው ፕሮጀክት ዋና ዳይሬክተር በመሆን ስትሾም ታሪኩ ያሳያል።

*ክልክላ* የተሰኘው መጽሃፍም በ(2004 ዓ.ም) በዮርዳኖስ ሽፈራው የተጻፈ ሲሆን በረጅም ልቦለዱ ውስጥ ዋናዋ ገጸባህሪ ምንትዋብ ስትሆን በማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ከፍተኛ ሚና የምትጫወት ጠንካራ እንስት ናት። ምንትዋብ በራሷ ጥረት ያፈራቻቸው በረካታ ሀብቶች ባለቤት ስትሆን ከመኖሪያ ቤቷ ስንጀምር በጣም ዘመናዊና ሁሉ ነገር የተሟላለት ማለትም ከባለፎቅ የእንግዶች መቀበያ ጀምሮ የመዋኛ ገንዳ፣ የሰራተኞች መኖርያ፣ የጥበቃ ቤት፣ የአትክልት ቦታዎችን ያካተተ ከመሆኑም በላይ ራሷ የምታስተዳድራቸው አራት የንግድ ድረጀቶችም አሏት። ምንትዋብ በስራዎቿ ብቁና ለማንም ጥገኛ ያልሆነች በራሷ የምትተማመን

ጠንካራ ገጸባህሪ ናት። ምንትዋብ በግቢዋና በድርጅቶቿ ውስጥ በርካታ ሰራተኞችን የምታስተዳድርና በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ በንቃት የምትሳተፍ፣ የተቸገረን የምትረዳ፣ ሆደ ቡቡ ሴት ናት። ነገር ግን ከእሷ ትዕዛዝ ውጭ የሚሆን ካለ በተለያዩ የቅጣት አይነቶች አደብ የምታስገዛ እልኸኛ ሴት ናት። ምንትዋብ ምንም እንኳ የተትረፈረፈ ሃብት ቢኖራትም ህመም የሚጸናባት በመሆኑ ሀብቷን ለመውረስ የሚያሰፈስፉት ደግሞ በርካቶች ናቸው። ከነዚህ መካከልም ትርሲትና ግርማ ዋነኞቹ ናቸው። ግርማ የምንተዋብ እጮኛ ሲሆን ለአራት አመታት ያህል በፍቅር አብረው ኖረዋል። ግርማ ከምንትዋብ በአስር አመት ያህል በእድሜ የሚያንስ ሲሆን የቀረባትም አግብቷት ገንዘቧን ለመውረስ ነበር። ይሁን እንጅ የምንትዋብ ጋብቻውን ቶሎ አለመቀበል ጋብቻው እንዲጓተትና ሲቋምጥለት የነበረው የሃብት ጉዳይ እንደጉም በኖ እንዲጠፋ አድረጎታል። በመጨረሻም የወ/ሮ ምንትዋብ ህይዎት በማለፉ ምክንያት ግርማ በትርሲት አማካኝነት ከምንትዋብ ቤት ተባርሮ ሃብቷ ግን ትርሲት እንድታስተዳድረው ሆነ የሚል ታሪክ አለው።

## 3.2. ትንተና

በዚህ ምዕራፍ፣ በምዕራፍ አንድ በገለጽኳቸው የመተንተኛ ስልቶች፣ በምዕራፍ ሁለት በተደራጁ ንድፍ ሀሳቦች መሰረት ታላሚ ረጅም ልቦለዶችን ለመተንተን ተሞክሯል። በአሰፋ በቀለ *ምዕራባዊት* እና በዮርዳኖስ ሽፈራው *ክልክላ* ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የተነሱ የሴትነት ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ ዓባዊ ስርዓቱ ከኢኮኖሚያዊ፣ ከማህበራዊና ከመደብ አንጻር በምን መልክ እንደቀረበ ለመተንተን ተሞክሯል።

### 3.2.1. ዓባዊ ሥርዓት

ዓባዊ ሥርዓት በማህበረሰቡ ዘንድ ሴቶችን የበታች አድርጎ ሲቆጥር የነበር የቆየ አመለካከት ሲሆን ይህም በማህበረዊ፣ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ የወንዶችን የበላይነት ያረጋገጠ ነበር። ቴዎድሮስ ገብሬ (2001) እንደሚገልጸው ‹‹አባዊ ሥርዓት የተባዕት የበላይነት አንዳንዴም ተጫኝነት እና ጨቋኝነት የሰፈነበት ማህበራዊ ሥርዓት መጠሪያ ነው። በዚህ ሥርዓትም የሴቶች እንቅስቃሴ በወንዶች የተገደበ ነው ሲል ይገልጻል። ሃሳቡ እንደሚያሳየውም ዓባዊ ሥርዓት እውናዊ በሆነው የማህበረሰቡ ኑሮና በበርካታ የሥነጽሑፍ ሥራዎች ላይ ለዘመናት የወንዶችን የበላይነት ሲያንጸባርቅ የቆዬ መሆኑንና ይህም ሴቶች ማንኛውንም ስራ እንዳይሰሩና መብተቸውን እንዳያስከብሩ ቀፍድዷቸው መሆኑን ነው። ይሁን እንጅ

በምዕራባዊትና ክልከላ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ሴት ገጸባህሪያት ይህንን ሥርዓት ተቃውመው አላስፈላጊነቱንም በተግባር አሳይተዋል፡፡

በዓባዊ ሥርዓት አስተሳሰብ ሴት ልጅ ወንድ ልጅን ላግባህ ብላ መጠየቅ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደነውር የሚቆጠርና እስከመገለል ድረስ ሊያደርስ የሚችል ነው፡፡ ይህን የማህበረሰቡ የተሳሰተ ግንዛቤ በማስወገድ በምዕራባዊት ረጅም ልቦለድ ውስጥ የምትገኘዋ ምዕራባዊት በማህበረሰቡ ዘንድ እንደነውር የሚቆጠረውን ባህል በመጣስ የፈለገችውን የትዳር አጋር አግባኝ ብላ ስትጠይቅ እናያታለን፡፡ ማስረጃ  እንመልከት፡-

> ይሰማኛል አቶ አካሉ፤ እንግዳ ነገር፤ እንግዳ በሆነ መንገድ ሲገጥም መደንገጥ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ያልጠበከውን ነገር በማትጠብቀው ሁኔታ ሴቷ ልጅ <u>“አግባኝ” ብዬ እየጠየኩህ ነው፡፡</u> ያ ሁሉ ሆኖ  ሰውየው አንተ በመሆንህ ብቻ <u>እነሆ በባህላችን ለሴት ልጅ እንደታላቅ ውርደት የሚያስቆጥረውን እርምጃ ወስጄ አግባኝ እያልኩህ ነው፡፡</u> በሚገባ አውቅሃለሁና “ለምና አገባችኝ” ብለህ እንደማትመጻደቅ አውቃለሁ፡፡ በራሴም በኩል የሴትነት ደረጃዬን አውቀዋለሁ፡፡ ማንም ሊመሰክርለት የሚችል ቁንጅና አለኝ፡፡ ምግባሬም መልካም ነው፡፡ ብዙ ያልተማርኩ ቢሆንም  ጥሩ ማሰብ እችላለሁ፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ምዕራባዊት፣ 26-27)፡፡

ምዕራባዊት በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን አባዊ የሆነ ኋላ ቀር አስተሳሰብ በመጣስ በከፍተኛ የራስ መተማመን ስሜት በድፍረትና በኩራት አግባኝ ትለዋለች፡፡ ይህም የሚያሳየው ሴቶች ምን ያህል የጸረ-ዓባዊነት ትግል እያደረጉ መሆኑን ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ አባዊ ስርዓቱን የሚጠብቅ ደንብ ይመሰርታል፡፡ ይህም ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ ጥሩ አይደለም ብሎ የሚያምንበትን እንደነውር በመቁጠር ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲወገዝ በማድረግ በሴቶችና በወንዶች መካከል ድንበር በማበጀት ከለላ ያስቀምጣል፡፡ ማህበረሰቡ ያስቀመጠውን ደንብ የምትጥስ ሴት ስትወገዝ ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ እንደመጥፎ ሴት እንድትታይ ስትደረግ ቆይታለች፡፡ ሴቶች በወንዶች ታጭተው እንጂ አጭተው ማግባት ክልክል በሆነበት ሁኔታ ምዕራባዊት አባዊ ስርዓቱን በመጣስ ሴቷ ወንዱን መጠየቋ የሴቶችን የተሻለ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ነው፡፡ ምዕራባዊት ወንዶችንና ሴቶችን በተግባር አራርቆ የቆየው የአባዊ አስተሳሰብ በማፍረስና በመቃወም ያሰበችውን ታደርጋለች፡፡ ምክንያቱም አባዊ ስርዓት ወደ ኋላ እንጂ ወደፊት የማያራምድ የሴቶችን ችሎታና መብት የሚጋፋ የአንድን ወገን ብቻ የበላይነት

የሚያንጸባርቅ በመሆኑ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አመዝኖ ስለታያት ነው፡፡ ስለዚህ የምዕራባዊት ዓባዊ ሥርዓትን ተቃውሞ መውጣት አንድም ሴቷ የፈለገችውን የማድረግ መብቷን የሚያጠናክር በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች እያካሄዱት ባለው የጸረ-አባዊነት ትግል ወንዶችም ተጠቃሚ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ይህንን ሃሳብ በመደገፍም Tyson (2006) ዓባዊ ስርዓት ሴቶችን ብቻ ሳይሆን ወንዶችንም ተጎጂ ያደርጋል፤ በማለት ታስረዳለች፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት አባዊ አስተሳሰብ ለወንዶች ያዳላ ቢመስልም አብዛኛውን ሀላፊነትና ተግባር በወንዶች በመጣል ጫና አድርሶባቸው የቆየ ስለሆነ ነው፡፡ በተመሳሳይም በክልከላ ረጅም ልቦለድ ስንመለከት፡-

> ወ/ሮ ምንትዋብ ከቁንጅናም በላይ የሚለብሰውን፤ የሚናገረውንና የሚበላውን የሚመርጥ ወንድ ይወዳሉ፡፡ በሁለቱ ተፋቃሪዎች መካከል ያለው የእድሜ ልዩነት <u>አስር አመት </u>ገደማ ይሆናል፡፡ ምንትዋብ በሃምሳዎቹ መጨረሻ ላይ ያሉ ሲሆኑ ግርማ ደግሞ የአርባዎቹን የእድሜ ክልል እየጨረሰ ይገኛል፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣2)፡፡

በዓባዊ ሥርዓት አስተሳሰብ ጋብቻ የሚፈጸመው ወንድ ልጅ ከሴት ልጅ በእድሜ ከበለጠ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ለአዳም አጋርነት የተሰጠችው ሄዋን በአስራ አምስት አመት እንደምታንስ ይገልጻል፡፡ ይህም ለዘመናት ማህበረሰቡ አምኖበት በመቆየቱ ሴቶች የፈለጉትንና የወደዱትን እንዳያገቡ በእድሚያቸው ምክንያት ተጽዕኖ ሲፈጠርባቸው ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ምንትዋብ ይህንን ተጽዕኖ በመስበር በእድሜ ከእሷ በአስር ዓመት ያህል የሚያንሰውን ግርማን ወዳውና አፍቅራው ለአራት አመታት ያህል አብራው ቆይታለች፡፡ ስለዚህ የምንትዋብ ውሳኔና ተግባር ለትዳር እድሜ እንቅፋት ሊሆን እንደማይገባና ሴቶች የፈለጉትን የትዳር አጋር መርጠው ማፍቀርና ማግባት እንደሚችሉ አስረጂ ነው፡፡

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም (1978) አባዊ ሥርዓት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በቤተሰብ ኑሮ ረገድ የወንድ የበላይነት የሰፈነበት የጥንት ማኅበረሰብ ሥርዓት ነው፡፡ ወንዶች የሀላፊነት ቦታዎችን እንዲያገኙ የበለጠ እድል አላቸው፡፡ የቤተሰብ መሪ፣ የማህበራዊ ቡድኖች መሪዎች፣ የሥራ ቦታ አለቃ በመሆን በትልልቅ ቦታዎች የስልጣን የበላይነቱን ይይዛሉ በማለት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጅ በልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙት ዋናዋና ሴት ገጸባህሪያት ይህንን ገለጻ በመሻር ቤተሰብ ሲመሩ፣ በተለያዩ የስራ ዘርፎች ሲሰማሩ፣ ትላልቅ የንግድ ቦታዎችን በብቃት ሲያስተዳድሩ፣ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ራሳቸውን ችለው በንቃት ሲሳተፉ ይታያል፡፡ ማስረጃ እንመለከት፡-

> ግርማ ምግብ ይወዳል። ምግቡ በሚፈልገው ደረጃ ካልተሰራለት ደግሞ ጎደለ የሚለውን ጥራት ዘርዝሮ ለምንትዋብ ሪፖርት ያደርጋል። ስለዚህ በተለይ ምንትዋብ በሌሉበት የሚካሄደው ግርማን እራት የመመገብ ሥነሥርዓት በጥንቃቄ ነው የሚካሄደው። ምንትዋብና ግርማ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እራት አብረው አይበሉም። ምንትዋብ ሥራ ቦታቸው አምሽተው የሚገቡ ሲሆን ግርማ ቀደም ብሎ ገብቶ፤ ገላውን ታጥቦ፤ እራቱን በልቶና ጣጣውን ጨርሶ ነው የሚጠብቃቸው። (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣11)።

ምግቡ በሚፈልገው ደረጃ ካልተሰራለት ደግሞ ጎደለ የሚለውን ጥራት ዘርዝሮ ለምንትዋብ ሪፖርት ያደርጋል የሚለው ማሳያ አንድም የቤቱ አባውራ ምንትዋብ እንደሆነች የሚያስረዳ ሲሆን ሌላው ነገሮችን የማስተካከል ስልጣንም ራሷ እንደሆነች አመልካች ነው። በዓባዊ አስተሳሰብ ሴት ወደ ማጀት ወንድ ወደችሎት የሚለውን የማህበረሰቡ አባባል በመጣስ ስራዋን እስከ አራትና አምስት ሰዓት አምሽታ አስክትመጣ ድረስ ወንዱ ልጅ በቤት ውስጥ ገላውን ታጥቦ፤ ራቱን በልቶና ጣጣውን ጨርሶ ይቆያታል። ይህ የሚያሳየው በቤት ውስጥ የሚቆያት ግርማ አደባባይ ወጥቶ ስራ ሲሰራ ሳይሆን በምንትዋብ ቤት ውስጥ ሁኖ ውበቱን ሲጠብቅና የምግብ ፍላጎቱ እንዲሟላለት ሲጥር እናየዋለን። ግርማ የምንትዋብ ጥገኛና የመስራት አቅም የሌላው ነው። ምንም እንኳን በምንትዋብ ቤት ይኑር እንጅ በቤት ውስጥ የማዘዝ መብት የሌላው ለምንትዋብ በወሬ አቀባይነት የሚታወቅ ነው። ምንትዋብ ከሥራ ቦታ አምሽታ ቤቷ እስክትገባ ድረስ አልጋ አሟቂ እንጂ ምንም ዓይነት ተግባር የሌለው ገጸባህሪ ሁኖ እናገኘዋለን። ይህም የሚያሳየው የዓባዊ ሥርዓቱን መጣስና ሴቶች ምንያህል ጠንካሮች መሆናቸውን ነው።

Keith Green and Jill Le Bihan (1996) ዓባዊ ሥርዓት በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳዮች በቋንቋ ውክልናም ጭምር ወንዶችን የበላይ አድርጎ የቆየ አዕምሯዊና በተግባርም ሲገለጽ የነበረ ሥርዓት ነው በማለት ይገልጻሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ማሳያ ስንመለከት፡-

> ‹‹ሳምሶን የሃያ ሰባት አመት ወጣት ነው። አንዳንድ ጊዜ ይሞክር የነበርውን የድለላ ስራ እርግፍ አድርጎ ከተወ ወዲህ ሙሉ ለሙሉ ስራ ፈት ሆኗል። የቤት ኪራይ ክፍየውን፣ የምግብ ወጭውን፣ ልብሱን፣ ጫት መቃሚያውን፣ መጠጫውንና የኪስ ገንዘቡን ሁሉ የምታሟላለት ትርሲት ናት።›› (ክልከላ፣56)።

በቀደምት ዘመናት ሴቶች የወንዶች የበታች ተደርገው ይቆጠሩ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። ይሁን እንጅ ይህን ታሪክ በመቀየር ሳምሶን የትረሲት የኢኮኖሚ ጥገኛ መሆኑን ከማስረጃው ማየት ይቻላል። ሙሉ ለሙሉ ስራ ፈት ሆኗል የሚለው አረፍተ ነገር የሳምሶንን ስንፍና እና

እራሱን እንኳን ማስተዳደር የማይችል፣ ተረጂ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህም የሚያሳየው ሴቶች ወንዶችን የማስተዳደር፣ የመግዛትና የመምራት ብቃት መኖራቸውን ነው፡፡

ዓባዊ ሥርዓት ወንዶችን የቤተሰብ መሪ፣ የማህበራዊ ተቋማት መሪዎች፣ የሥራ ቦታ አለቃዎችና የመንግስት መሪዎች በመሆን ትልልቅ የሀላፊነት ቦታዎችን የማግኘት የበለጠ እድል አላቸው፡፡ በምዕራባዊትና በክልከላ ውስጥ ግን ይህ ነገር ተቀባይነቱን ሲያጣ እናስተውላለን፡፡ በአስረጅ ስንመለከትም፡-

"… የሁሉም ነገር መሪና አስተባባሪ ግን አሁንም እሷ! አዎ፣ ራሷን እንደሻማ አቅልጣ የሌሎቹን ኑሮና ሕይዎት በጽኑ መሰረት ላይ የገነባችው ምዕራባዊት ጌታቸው" (አጽንኦቱ የእኔ፤ ምዕራባዊት፣221)፡፡

አስረጂው እንደሚያሳው ምዕራባዊት የሁሉም ነገር ሰሪ መሪ በመሆን ራሷን መስዋዕት አድርጋ ሌሎች እንዲኖሩ የምታደርግ አባዊ ስርዓቱን በአስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የምትፋለም መሆኗን ነው፡፡

በዓባዊ ሥርዓት አስተሳሰብ ሴት ልጅ መብታቸው ሲጣስ አልቅሰው በእንባቸው ከመግለጽ ውጭ መፍትሄ አልነበራቸውም፡፡ በምዕራባዊት እና በክልከላ ውስጥ የሚገኙት ምዕራባዊትና ምንትዋብ የተሰኙት ዋና ዋና ሴት ገጸባህሪያት ግን በደል ደረሰብን ብለው ካሰቡ እንደማነኛውም ሴቶች የሚያለቃቅሱ ሳይሆኑ መብታቸውን ለማስከበር የማይደራደሩ ጀግና ሴቶች ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያነት፡-

> "አሁን ግን ምንም እየሰራህ እንዳልሆነ ሊገባህ ይገባል"
>
> "ማለት?"
>
> "ወንጀለኛ አልያዝክማ! እኔው እራሴ ሰው ጠፋብኝ፤ አዳጋ እንዳይደርበት ክትትል ይደረግልኝ ባልኩ አይደል ያሰርከኝ!? ወንጀል ፈጽማለች ብሎ የጠቆመህ አለ?" አለችው፡፡
>
> "ይኽ እኮ ወንጀለኞች የፈጸሙትን ወንጀል ለማድበስበስ የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው!" አላት ፖሊሱ ኮራ ፈገግ እያለ፡፡
>
> "ጥሩ ተምረሃል፤ ነገር ግን ይህን ዓይነት ድርጊት የሚፈጽሙት ሰዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ ለመለየት የተግባር ልምምድ ይጎድልሃል" ትንሺም ቢሆን ህግ አውቃለሁ አንተ ግን ከህግ በላይ ሆነህ በእብሪት መወጠርህን ላስታውስህ ብዬ

ነው፡፡ ህግ አክባሪ ብትሆን ኖሮ ገና በተጠርጣሪነት ደረጃ ላይ እያለሁ እጆቼን የፊጥኝ ባላሰርከኝ ነበር፡፡ ይገባሃል"? (አጽንኦቱ የእኔ፤ ምዕራባዊት፣164)፡፡

ምዕራባዊት አልቅሳና አንገቷን ደፍታ ዝም የምትል ሳትሆን ትክክል ነው ብላ ላመነችበት ነገር ወደኋላ የማትል አንደበተ ርዕቱ ሴት ነች፡፡

ምዕራባዊትና ምንትዋብ ሴት ልጆች መብታቸው ሲጣስ አልቅሰው በእንባቸው ከመግለጽ ውጭ መፍትሄ የላቸውም የሚለውን የተዛባ አስተሳሰብ ተቀባይነቱን በማሳጣት ራሳቸውን ከፖሊሶች በማስበለጥ ከእነሱ በተሻለ መብታቸውን ለማስከበር ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ በሳል ንግግር ሲያቀርቡ ይታያል፡፡ ከዚህም ባሻገር በማህበራዊ መስክ የሴቶች ሚና ወይም የስልጣን ክፍፍል ጾታን መሰረት ያደረገ ሳይሆን የግለሰባዊ ችሎታን መሰረት ማድረግ እንዳለበት በተግባር ያሳዩ ናቸው፡፡ ይህ የአባዊ ስርዓት አስተሳሰብ በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ ዘርፍ እንዲሁም በመደብ እንዴት እንደተንጸባረቀ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

### 3.2.1.1. የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ድርሻ

ለሁሉም ነገር መሰረቱ ገንዘብ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶች ገንዘብ እንዳያፈሩ በቤት ውስጥ ብቻ ተሸብበው ቆይተዋል፡፡ ወንዶች ሀብት እያፈሩ ሴቶች ግን በቤት ውስጥ ሁነው ልጅን ማሳደግ እና የቤት ውስጥ ስራን ከመስራት ውጭ ምንም ሚና አልነበራቸውም፡፡ በተለያየ መንገድ ቤተሰብን የማስተዳደርና የገንዘብ አቅርቦት የማድርግ ኀለፊነት እንዳለው ተደርጎ ሲወሰድ የቆየው ወንድ ነበር፡፡ ምክንያቱም በቆየው አስተሳሰብ ሴት ልጅ እንደ ወንዶች ከቤት ወጥታ ስራ በመስራት ገንዘብ የማግኘት አቅም የሌላት ተደርጋ ስለምትቆጠር ነው፡፡

ይህንን ሃሳብ በመደገፍ Carol and Mark (1976) በ19ኛው እና በ18ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ስለሴቶች የነበረው ግንዛቤ ሴት ከቤት ወጥታ ስራ ለመስራት አቅሟ አነስተኛ መሆኑንና ትላልቅ ውሳኔዎችን ለመወሰን የግንዛቤ እጥረት እንዳለባት ተደርጎ ይታያል ሲል ይገልጻል፡፡ ይህ ገለጻ የሴቶችን ብቃት የማይለካ እና የወንዶችን የበላይነት ለማስጠበቅ የሚደረግ የማህበረሰቡ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው፡፡ ሥነጽሁፍ የማህበረሰቡን የለውጥ ሂደትና እውነታ የሚያሳይ በመሆኑ *ምዕራባዊት* እና *ክልክላ* ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ሴት ገጸባህሪያት ይህን የተሳሳተ ግንዛቤ ፉርሽ በማድርግ ሴቶች በሁሉም ዘርፍ ተሰማርተው መስራትና ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ አሳይተዋል፡፡ ማስረጃዎችን ስንመለከትም፡-

"ምዕራባዊት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር የጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ናት። መንገድ ላይ አግኝታ የሳመቻት ደግሞ የእሷ ረዳት የሆነችው የሕግ ባለሙያዋ ትርሲት አያሌው" (ምዕራባዊት፣4)።

አስረጂው የሚያሳየው የልቦለዱ ዋና ገጸባህሪ የሆነችው ምዕራባዊት "ወንድ ወደችሎት ሴት ወደማጀት" የሚለውን የማህበረሰቡን ብሂል ተከትላ በቤት ውስጥ የምትልሞሰሞስና የወንዶችን ድጋፍ የምትሻ ሳትሆን ስራዋን በአግባቡ የምትሰራ ከዚያም አልፎ በሃለፊነት ቦታ ላይ በመቀመጥ አንድን ግዙፍ ተቋም የምትመራና በአግባቡ የምታስተዳድር መሆኑን ነው። ይህም ሴቶች በሀላፊነት ቦታ ላይ መስራት አይችሉም፣ የቤት ውስጥ ስራ ብቻ መስራት አለባቸው የሚለውን የተሳሳተ ግንዛቤ በመለወጥ ጠንካራ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ተጨማሪ ማሳያ ስንመለከትም ለሌላ አዲስ ሃላፊነት ስትሾም በሚከተለው መልኩ እናያታለን።

> ድርጅቱን የማቋቋሙ ስራ ሲፋጠን ቆይቶ እነሆ ‹‹ትኩረት ለቤተሰብ የእርዳታና የምክር አገልግሎት ድርጅት›› በሚል ስም ተቋቁሞ ሕጋዊ ፍቃድ አግኝቷል። ጠቅላላ ጉባዔ ተመስርቶ ጊዚያዊ የስራ አመራር ቦርድም ተመርጧል። የቀረው ዋና ዳይሬክተር መሾም ብቻ ነበር፤ እሱም ቢሆን በቅርቡ ተገኝቷል አለና ቀኝ እጁን ወደኮቱ ኪስ እያስገባ ምዕራባዊትን ፈገግ ብሎ ያያት ጀመር። አንድ ማንገቻ ያለው ባጅ መሳይ ነገር አወጣና በሁለት አጆቹ ፈልቀቅ አድርጎ በመያዝ ‹‹ይህን የዋና ዳይሬክተርነት መለያ ባጅ ለአዲሱ ድርጅት ስራ አስኪያጅነት በተመረጠው ሰው አንገት ላይ ላስገባው ነው። እናንተም እጆቻችሁን ለጭብጨባ አትጓቸው›› አለና ‹‹ምዕራባዊት ጠጋ በይኝ›› አላት። […] አንገቷን ሰጠችው። አጠለቀላት። (አጽንኦቱ የእኔ፤ ምዕራባዊት፣219)።

ምዕራባዊት በምትሰራው ሥራ ሁሉ ውጤታማ የሆነች ጠንካራ ገጸባህሪ ናት። በዚህ ጥንካሬዋ ደግሞ በተለያየ የስራ መስክ ላይ በዋና ስራ መሪነት ትመረጣለች። ይህም ተግባር የሚያመለክተው የማህበረሰቡን የለውጥ ሂደት ሲሆን ሴቶች በየትኛውም ዘርፍ ቢሰማሩ ውጤታማ በመሆን ለአንድ ሀገር እድገት ጉልህ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውን ነው። ስለሆነም ይህ ተግባር ሴቶችን የሚያበረታታ እና ዓባዊ የሆነውን የኢኮኖሚ ሥርዓት ግንዛቤ ማስተካከል የሚያስችል እንደሆነ ማሳያዎቹ አመላካች ናቸው። ምክንያቱም ምዕራባዊት የሴቶችን ጥገኝነት የማትቀበል፣ በአላማዋ የጸናችና ሙከራዋ ሁሉ የሚሳካላት ሴት ናት። ይህም ሴቶችን ይጨቁን የነበረውን ባህል በመተው የራሳቸውን አካሄድ መከተላቸውንና ከተጽዕኖ መውጣታቸውን ያሳያል። በተመሳሳይም ክልከላ በተሰኘው ርጅም ልቦለድ ውስጥ የምትገኘው ዋና ገጸባህሪ ምንትዋብ አባዊ በሆነው ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ተቀፍድዳ ቁጭ ያለች አይደለችም። ምንትዋብ

ሴትነቷ ሳይገድባት በተለያዩ ስራዎች ተሰማርታ የምትሰራና የብዙ ሃብቶች ባለቤት በመሆን ዘመኑ የሚፈቅደውን ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ በመከተል በቅንጦት የምትኖር ናት፡፡ ለዚህም ማሳያነት፡-

> የምንትዋብ የባለሀብትነት አንዱ መገለጫ የሆነው መኖርያ ቤታቸው ግዝፈቱና ውበቱ [...] ከመሬቱ ጀምሮ በየፎቆቹ ላይ ያለው ሰፋፊ በረንዳ፣ የግቢው ስፋት፣ የአረንጓዴ ቦታው ሳርና አበባ ውበት፣ የራሱ የተዋበ አጥር ያለው መዋኛ ገንዳውና በዙሪያው የተዘረጉ ምቹ አልጋ መሳይ ወንበሮች፣ ባለቀለም ግርዶሽ ያለው ሰፊ የመኪና ማቆሚያው፣ በቤቱ ጀርባ ያለው ባለፎቅ የእንግዶች መቀበያ እና የሰራተኞች መኖርያ፣ በቆንጆ ቅርጽ ተቀርጾ በተመሳሳይ ቀለማት የተዋበው የጥበቃው ቤት ብቻ ሁሉንም ደማምሮ ሲያየው <u>አቅም ያለው የሀገር ኢንባሲ</u> ወይም <u>ባለብዙ ኮከብ ሆቴል</u> እንጂ የግለሰብ መኖሪያ ቤት አልመሰለውም፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣53)፡፡

ዓባዊ የሆነው ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የወንዶች የበላይነትና እና የሴቶች የበታችነት የነገሰበት ሲሆን ወንዶች የኢኮኖሚውን የበላይነት ለዘመናት ይዘውት ኖረዋል፡፡ በሥነጽሁፍ ስራዎችም ውስጥ ሴቶች በከፍተኛ የኢኮኖሚ ደርጃ ላይ ሳይሆን የሚወከሉት ቤት ውስጥ ያሉ ሥራዎችን በማክናወንና ልጆችን በመንከባከብ ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ሴቶች እንደወንዶች በተለያዩ ዘረፎች የማይሰሩና የችሎታ ማነስ ኑሮባቸው ሳይሆን አባዊ የሆነው ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ተፅጽኖ ስላሳደረባቸው ነው፡፡ ምንትዋብ ማህበረሰቡ የሴቶች ድርሻ ብሎ በፈረጀው ባህል ውስጥ የምትልሞሰሞስ ሳትሆን ከወንዶችም ልክ እንደ ጠንካራዎች እኩል የምትሠራ የብዙ ሃብቶች ባለቤት የሆነች ገጸባህሪ ናት፡፡ ምንትዋብ ቤቷንም ሆነ ድርጅቶቿን በበላይነት የምትመራና የምታስተዳድር ስትሆን ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም በእሷ ሀላፊነትና ቁጥጥር ውስጥ እንደሆኑ የልቦለዱ ታሪክ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ልዩነት ስነሕይዎታዊ ብቻ እንጂ ከመስራትና ከማግኜት ጋር የተያያዘ ባለመሆኑ ሴቶች በየትኛውም ዘርፍ ተሰማርተው መስራትና ውጤታማ መሆን የሚችሉ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

Bengsten (1977) ሴቶች በካፒታሊዝም ስርአት ውስጥ በጥቃቅን ስራዎች የሚሳተፉ ቡድኖች ናቸው፡፡ ትላልቅ ስራዎችን የመምራት አቅም የላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ የመሳተፍ እድሉን ተነፍጓቸው ቆይቷል፡፡ በስነጽሁፎችም ይሁን በሚነገሩ ታሪኮች ሴቶች የመምራት አቅም የላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ በትላልቅ የኢኮኖሚ ተቋማት ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው በማለት የምትገልጸው የሴቶችን የስራ ሁኔታና የኢኮኖሚ ደረጃ የሚለካ አለመሆኑን ሴት ገጸባህሪያት በሚሰሩት ጠንካራ ስራና ሀላፊነት እንዲሁም በሚያመጡት ጥሩ ውጤት ማስመስከር ችለዋል፡፡

ስለሆነም ሴቶች በኢኮኖሚው መሳተፋቸው የሴቶች ትግል ውጤት ማምጣቱን ፍሬ ማፍራቱን ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም ሥነጽሑፍ እውነታን ያንጸባርቃል ከተባለ በውስጡ የሚነሱ ጉዳዮች የሰዎችን የዕርስበዕርስ ግንኙነት በማሳየት ያለውን ለውጥ ማጽናት ነው፡፡ ይህንንም ለማሳየት ያህል፡-

> እኔስ ከቦዘኔየ ጋር የምኖረው ስለምወደው ነው፡፡ አንተ አለህ አይደል እንዴ ለገንዘብ ብለህ በየቀኑ ገላህን የምትቸረችር፡፡ ታጥቦና ተቀባብቶ፤ ከስራ እስክትመለስለት ድረስ የእናቴን አልጋ ሲያሞቅ የሚያመሽ ቦዘኔ ቢያንስ በሌላ ቦዘኔ አያላግጥም፡፡›› …(አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣89)፡፡

ምንትዋብ የበርካታ ድረጅቶች ባለቤት በመሆኗ በርካታ ሰዎችን በገንዘቧ ታንበረክካለች ከነዚህም ውስጥ አንዱ ግርማ ነው፡፡ ግርማ በስራው ጠንካራ ሳይሆን የምንትዋብን የገንዘብ ድጋፍ ፈልጎ የሚኖር የኔ የሚለው ሀብት የሌላው ጥገኛ ወንድ ነው፡፡ በመሆኑም ግርማ ልክ እንደ ቤት ሰራተኛ ቤት ለቤት በመዋል ከስራ አራትና አምስት ሰዓት አምሽታ የምትመጣውን ሴት የሚጠብቅ ተረጂ ነው፡፡ ስለሆነም የግረማ ቤት መዋልና የምንትዋብ ስራ አምሽቶ መግባት ሙሉ ለሙሉ የነበረውን አባዊ የሴቶች አስተሳሰብ ውድቅ መሆኑን የሚያስረዳ ተግባር ነው፡፡ ሌላው ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል መስራት ብቻ ሳይሆን የበላይ ገዢ መሆን እንደሚችሉም ምንትዋብ ታሳየናለች፡፡ በሌላ አገላለጽ ቤት ውስጥ መስራትና መዋል የሴቶች የተሰጠ ሳይሆን ግርማንና በልቦለዱ ውስጥ የሚገኙ መሰል ወንዶችንም ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ግርማ ገላውን ለሴቶች አሳልፎ በመስጠት የገንዘብ ማግኛ እንዳደረገው ያመለክተል፡፡ ይህ ማለት ሴቶች ውበታቸውን እንደ አንድ የገቢ ምንጭ ይጠቀሙበታል በማለት ሲቀነቀን የቆየውን እሳቤ በወንዶችም የሚንጸባረቅና በተግባርም እንደሚያሳዩት ለግረማ የቀረበው ማሳያ አስረጂ ነው፡፡ ሴቶች ወንዶችን የማንበርከክና የመጫን ሀይል እንዳላቸው ከምንትዋብ ተግባር መረዳት ይቻላል፡፡ የሴቶች ተሳትፎ በኢኮኖሚው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ጉዳዮችም የተሻለ ብቃት እንዳላቸው መረዳት ያቻላል፡፡

#### 3.2.1.2. **የሴቶች ማህበራዊ ተሳትፎ**

የሰዎች አኗኗር ስልት የሚገለጽበት ባህል በተለያዩ ገጽታዎች ይንጸባረቃል፡፡ በዚህም ሰዎች በሚኖራቸው የዕርስበዕርስ ግንኙነት ወቅት የበላይነትና የበታችነት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ባህላዊ የጾታ ሚና ለወንዶች የሚያዳላ እና ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የሚመለከት ነው፡፡ ይህን ሃሳብ በማጠናከርም Tyson (2006) ባህላዊ የሴቶች ሚና ወንዶችን እንደ አስተዋይ፣ ጠንካራ፣

ተከላካዮችና ወሳኝ እንዲሁም ሴቶችን እንደ ስሜታዊ፣ ደካማ፣ ድጋፍ ፈላጊዎችና ተሸናፊዎች አድርጎ ያያል በማለት ታስረዳለች፡፡ እነዚህ የጾታ ሚናዎች በተገቢው መንገድ ልዩነቶችን እንዲገልጹ ተደርገው ላለፉት ዘመናት ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጅ ባህል እንደማህበረሰቡ ግንኙነት ሊሻሻልና ሊቀየር የሚችል በመሆኑ ይህን ሴቶችን ከወንዶች አሳንሶ የማየት ባህል በማሻሻል ሴቶችን በእኩልነትና በበላይነት በማቅረብ ምዕራባዊትና ክልከላ ረጅም ልቦለዶች በዋና ዋና ሴት ገጸባህሪያት አማካኝነት አሳይተዋል፡፡ ለዚህም ማሳያዎች በማቅረብ እንመልከት፡-

"የሁሉም ነገር <u>መሪና አስተባባሪ</u> ግን አሁንም <u>እሷ!</u> አዎ፣ ራሷን <u>እንደሻማ አቅልጣ</u> የሌሎቹን ኑሮና ሕይዎት <u>በጽኑ መሰረት</u> ላይ የገነባችው ምዕራባዊት ጌታቸው" (አጽንኦቱ የእኔ፤ ምዕራባዊት፣221)፡፡

በአብዛኛው የማህበረሰባችን ክፍል ወንዶችን የቤተሰብ ሃላፊ፣ ሴቶችን ደግሞ ጥገኛና ህጻናትን አሳዳጊ ብቻ አድርጎ ማሰብና ይህንኑ ሚና እንዲጫወቱ መገፋፋትና ማስገደድ በማህበራዊ መስክ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ በማጀት ብቻ እንዲሰማሩ የሚደረጉት ሴቶች ከወንዶች እኩል በማህበራዊ ጉዳዮች መስራት አይችሉም ብለው በመፈረጅ ነው፡፡ ነግር ግን ምዕራባዊት በማንኛውም ማህበራዊ ጉዳዮች በመሳተፍ እና ራሷን መስዋት በማድረግ የተበተነ ቤተሰብን በመሰብሰብ፣ የደፈረሰን በማጥራት፣ የተጣላን በማስታረቅና ሰዎች ትክክለኛውን መንገድ እንዲከተሉ በጽናት የምትሰራ ታታሪ ሴት ናት፡፡ ምዕራባዊት በተግባሯም ለሴቶች ብቻ ሳይሆን ለወንዶችም አርዓያ በመሆን መስዋዕትነት ትከፈላለች፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሴቶች የድኅነትና የመልካም ነገር ተምሳሌት መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላ ማሳያ ብንመለከት፡-

> ‹‹በሴት ልጅ ምክንያት ልቡ የተሰበረ ወንድ እድሜ ልኩን አጎንብሶ ሲሄድ ለማየት ትዕግስት አላገኘሁም›› አለችው፡፡
>
> ‹‹ማለት?›› አላት አቶ አካሉ ፍጥጥ ብሎ እየተመለከታት፡፡
>
> ‹‹ቀና እንዲል እፈልጋለሁ››
>
> ‹‹በምን ዘዴ?››
>
> ‹‹ዘዴና ብልሃት ሳይሆን ቁርጠኝነትን ይፈልጋል፡፡ እኔም ቆርጫለሁ፡፡››
>
> ‹‹ምን ለማድረግ?›› አላት አካሉ የባሰ እየደነገጠ፡፡

‹‹አዎ አቶ አካሉ ልብህ ክፉኛ መሰበሩ ገብቶኛል። ልጠግነውም ቆርጫለሁ። (ምዕራባዊት፣26)።

ምዕራባዊት የተባለችው ገጸባህሪ ራሷን መስዋዕት አድርጋ የሌሎች ህይወት እንዲስተካከል የምታደርግ ቆራጥና አይበገሬ ሴት ናት። አካሉ የተባለውን ገጸባህሪ በተለያየ ምክንያት ቤተሰቡ ሰላም አጥቶ ከሚስቱና ከልጆቹ ተለያይቶ የሚኖርን ሰው ከደረሰበት አስቸጋሪ ፈተና ለመታደግ ያላትን ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ያሳያል። በአለፉት ዘመናት ሴቶች የጥፋት ተምሳሌት እየተባሉ የሚፈረጁትን የማህበረሰቡ የተሳሳተ እሳቤ በማስወገድ ሴቶች መንፈሰ ጠንካራና ለያዙት አላማ ወደ ኋላ የማይሉ ጀግና መሆናቸውን ምስክር በመሆን አሳይታለች። ይህ የሚያሳየው የሴቶችን ቆራጥነትና ለቆሙበት አላማ አይበገሬ መሆናቸውንና ከምንም በላይ ከራሳቸው ይልቅ ለሌላ ሰው የሰላምና የድኅነት መንገድ መሆናቸውን ነው። አካሉ የተሰኘው ገጸባህሪ በሴት ልጅ ምክንያት የሞቀ ትዳሩን በመፍታት ከሚወዳቸው ልጆቹ ተለይቶ ሰው ሁሉ ለመኖር የሚጓጓባትን አዲስ አበባ ከተማን በመልቀቅ ወደጋምቤላ በመሄድ በብቸኝነት የስቃይ ኑሮን ሲኖር እናየዋለን። ይሁን እንጅ የፈረሰ ትዳሩና የተናጋ ህይዎቱ መልሶ በሴት ሲጠገን እናየዋለን። ይህም በመጻህፍ ቅዱስ ታሪክ በኦሪት ዘፍጥረት በምዕ 3: 8-24 ስለአዳምና ሄዋን ከተነገረው ጋር የሚመሳሰል ሆኖ እናገኘዋለን። አዳም በሄዋን አማካኝነት ከገነት እንደተባረረና ተመልሶ ደግሞ በድንግል ማርያም አማካኝነት ወደቀደመ ክብሩ እንደተመለሰ ይገልጻል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ሴቶች የጥፋት ተምሳሌት ሳይሆኑ የመዳን ተምሳሌቶች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። ይህንንም ምዕራባዊት ግልጽ አድርጋ ታሳየናለች።

ሴቶች በማህበራዊ ንቅናቂያቸው ምክንያታዊ አስተሳሰቦችን በመያዝ የወንዶችን የበላይነት በመቃወም ጾታዊ መድሎ እንዲለወጥ በቁርጠኝነት ትግል አድርገዋል በማለት Bellesy and Moore (1997) የገለጹት ሃሳብ ትክክል መሆኑን ምዕራባዊትና ምንትዋብ አመላካች ናቸው። የምዕራባዊት ጥንካሬ ከውጫዊ ዕይታ በተጨማሪ የሰዎችን ውስጣዊ ጉዳት በመርዳት ምን ያክል ማህበረሰቡን መርዳትና መፈወስ መቻሏን ነው።

Fischer, Patricia and Vianen (2004) በጥናታቸው ሴቶች ያላቸውን ስሜት በመከፋት፣ በፍርሃት፣ በሃፍረትና በጥፋተኝነት መንፈስ ሲገለጽ የወንዱ ግን በቁጣና በሌሎች መሰል ስሜቶች ይንጸባረቃል፤ በማለት የገለጹ ሲሆን ምዕራባዊትና ምንትዋብ ግን ሃሳቡን ተቀባይነት ያሳጡታል። ምክንያቱም ምዕራባዊትና ምንትዋብ መንፈሰ ጠንካራ፣ ምክንያታዊ፣ ቆራጥና ላመኑበት ነገር እስከ መስዋትነት ድርስ የሚደርሱ አይበገሬ ሴቶች ሆነው እናገኛቸዋለን።

ምዕራባዊት ለመብቷ የምትታገል፣ ትክክለኛውን መንገድ ይዛ የምትጓዝ ሴት በመሆኗ ማንንም የማትፈራ ምክንያታዊ ሴት አድርጓታል፡፡ ለዚህም እንደማሳያ  ምንመለከት፡-

> አንችም የአሶሳ ተወላጅ ከመሆንሽም በላይ የደርግ ወታደር ልጅ መሆንሽን እናውቃለን፡፡ [...] “የደርግ ወታደር አትበል!” አለችው  ቁጥት ብላ፡፡ “የእኔ አባት ኢትዮጵያዊ የጦር መሪ እንጂ የደርግ አሽከር አልነበረም፡፡” “ችግር የለውም፤ ነገር ግን አንች የአሶሳ ልጅ ሆነሽ ሳለ ከወሎየው አካሉ ልሳነ ወርቅ ጋር በምን ሁኔታ እህትና ወንድም ልትሆኑ ትችላላችሁ?” ሲል መስቀለኛ ጥያቄ ያቀረበ መስሎት ፈገግ እያለ ጠየቃት፡፡ “ችግርህ ምን እንደሆነ ይገባሃል? አንተ የምታውቀው ስለጋምቤላነት እንጅ ስለኢትዮጵያዊነት ስላልሆነ ነው፡፡ አሶሳና ወሎ የአንድ አገር ሁለት ግዛቶች እንጂ በቪዛ የሚተላለፍባቸው ሁለት አገሮች እንዳይመስሉህ!” አለችው፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ምዕራባዊት፣ 167)፡፡

ምዕራባዊት መብቷን ለመጋፋት በፖሊሱ ዘንድ የሚደርስባትን ጫና ለመታገል ምክንያታዊ የሆኑ ሃሳቦችን በማንገብ አላስፈላጊ የሆኑ ጭቆናዎችና እንዲሁም እንግልት በጽኑ በመቃወም ትታገላለች፡፡ ይህም የሆነበት አንድም የህግ ባለሙያ በመሆኗ እና ህግና ስርዓትን የምታውቅ በመሆኗ ነው፡፡ ሌላው በመሸነፍና በመልፈስፈስ ዝቅ በማለት በወንዶች አለመበለጧን ለማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም ምዕራባዊት በቁርጠኝነት ከተነሳችበት አላማ በተለያዩ መሰናክሎች ተስፋ በመቁረጥ ከግብ ሳታደርስ መቅረት እንደሌለባት በራሷ ስለምትተማመን ነው፡፡ ስለዚህ ምዕራባዊትን በማስፋራትም ሆነ የተለያዩ ጭቆናዎችን በማድረስ ዓላማዋን ለማደናቀፍ ቢሞክርም እንኳ ለማንም የማትበገርና የማትፈራ ሴት መሆኗን በምታቀርበው ምክንያታዊ ሃሳብና ቆራጥ ንግግር አሳይታለች፡፡

በማህበረሰቡ እሳቤ ሴቶች ልክ እንደ ወንዶች በማህበራዊ ግንኙነት መሳተፍ ለምሳሌ ማስታረቅ እንደማይችሉ ይታመናል፡፡ ይህም የሚሆነው ሴቶች ተናግረው ማሳመን አይችሉም በማለት በደካማነት በመፈረጅ ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ብርሀን (2009) ተመስገን (2004፡95) ጠቅሶ እንደገለጸው በዶኮ ጋሞ የእርቅ ሥርዓት ጊዜ ሴቶች አይታደሙም፡፡ ጉዳዩ የእነሱ ቢሆንም እንኳ በርቀት ተቀምጠው ሲጠየቁ ይናገራሉ፤ ወይም በስማ በለው ሃሳባቸው ይነገርላቸዋል እንጅ እነሱ ቀርበው አይናገሩም፡፡ የሴቶችን ሚና ዝቅ በማድረግ ወንዶችን እንደ አስተዋይ፣ ጠንካራ፣ ተከላካይና ወሳኝ እንዲሁም ሴቶችን እንደ ስሜታዊ ደካማ፣ ድጋፍ ፈላጊዎችና ተሸናፊዎች አድርጎ ማየቱን ነው፡፡  ሴቶችን በተለያዩ የእርቅ ስነስርዓት ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ አለመሆናቸው ነው፡፡ ነገር ግን ምዕራባዊት ጠንካራ የሆነች  ሰዎችን

በማስታረቅ የፈረሰን ቤተሰብ ራሷን ሰውታ ወደ ነበረበት የምትመልስ ትክክለኛ የቤተሰብ ድልድይ ናት። ለዚህ ማሳያ ብንመለከት፡-

> “የምፈልገውን የዕርዳታ አይነት ከመግለፄ በፊት በአካሉ ሕይዎት ዙሪያ እኔ ማድረግ የፈለግኩትን ነገር ብነግርህ!” አለችው።
>
> “እሺ!” አላት በጉጉት አይን እያያት። የለፋሁትን ያህል ለፍቼ፤ የደከምኩትን ያህል ደክሜ፤ አቶ አካሉን ከባለቤቱ በማስታረቅ የፈረሰ ቤቱን ላድስ፤ የተፈታ ትዳሩን ልቋጥርና የተበተነ ቤተሰቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ ጥረት ጀምሪያለሁ።” “እጅግ የተቀደሰ ሃሳብ ነው።” አላት ይርጋ። …(ምዕራባዊት፣ 103)።

ሴቶችን የሚመለከት የትኛውንም ያህል ጉዳይ ቢኖርም እንኳ በርቀት ተቀምጠው ሲጠየቁ ይናገራሉ፤ ወይም በስማ በለው ሃሳባቸው ይነገርላቸዋል እንጅ እነሱ ቀርበው አይናገሩም ነበር። ነገር ግን ምዕራባዊት በሁሉም ዘርፍ የበላይነቱን በመቆጣጠርና ውጤታማ በመሆን ሃሰቡን ውድቅ ታደርገዋለች። ለዚህም ማሳያው ይዛው የተነሳቸውን ሃሳብ ከግብ ስታደርሰውና ለፍሬ ስታበቃው በሚከተለው መልኩ እናገኛታለን።

> ‹‹ክቡራንና ክቡራት እንግዶቻችን፤ ከዛሬዋ ዕለት ላይ ለመድረስ መደረግ ያለበት ሁሉ ሲደረግ፤ መሆን ያለበት ሁሉ ሲሆን ቆይቷል። ጥረቱ ሁሉ በዛሬው ዕለት ለተፈጸመው ጉዳይ ሰለባል ስለነበር ሲሆንና ሲደረግ የቆየውን ሁሉ ከመዘርዘር ይልቅ ውጤቱን ማየት የተሻለ ይሆናልና እስቲ በአይን የሚታይ ነገር ካለ ልጋብዛችሁ›› አለችና ወደአካሉ እና መዓዛ ዞር ብላ ፈገግ አለች። […] ፊት ለፊት ተያዩና አካሉ ሁለት እጆቹን ወደፊት ሲዘረጋ መዓዛ በእቅፉ ውስጥ ገብታ ደረቱ ውስጥ ልጥፍ አለች። ልጆቻቸው ዙሪያቸውን ተጠመጠሙባቸው። (ምዕራባዊት፣216)።

የአካሉ ቤተሰብ የተፈታና ሰላም የጠፋበት ነበር፤ በዚህም ምክንያት ሀገር አስከ መልቀቅ ድርስ በመድረስ ልጆቹም የአባታቸውን ፍቅር እንዲያጡ እና በችግር እንዲሰቃዩ አድርጓቸዋል። ነገር ግን ይህን ችግር የተረዳችው ምዕራባዊት የቱንም ያህል ፈተና ቢገጥማት በብቃትና በበላይነት ተወጥታ ይህን የተበተነ ቤተሰብ መልሳ እንደነበረ አድረገዋለች። ይህ የሚያመለክተው ሴቶች ደካማ ናቸው፣ ምክንያታዊ አይደሉም፣ በሀሳብ ማሳመን አይችሉም የሚለውን የማህበረሰቡ አስተሳሰብ ስህተት መሆኑንና በተቃራኒው ነገሮችን ማስተካከል የሚችሉ ጥበበኛ፣ ለአላማቸው ቆራጥ የጀመሩትን ከግብ ሳያደርሱ የማያቆሙ፣ በነገሮች ተስፋ የማይቆርጡ የሰላም ተምሳሌት

መሆናቸውን ከምዕራባዊት ተግባርና ካመጣችውም  የተሳካ ውጤት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጨማሪ ማሳያ ስንመለከትም፡-

‹‹ቀድሞስ ቢሆን የአንድ አካሉን የተሰበረ ልብ ልጠግን የተነሳሁ ሴትዮ አምስት ልቦች ተሰባብረው እያየሁ ዝም የምል ከሆነ በየትኛው ህሌናዬ ሰው ልባል እችላለሁ? ሌላ ሰው ላያውቅብኝ ይችል ይሆናል፤ ህሌና ግን ሚዛኑ የራሱ ነው፡፡ አዎ እኔ! ማንም ሳያየኝ ራሴን እያየሁ ስሰቃይ መኖር የለብኝም፡፡ አካሉ የማዛ ነውና ላስረክባት ይገባል” አለች፡፡ (ምዕራባዊት፣ 62)፡፡

ምዕራባዊት በማህበራዊ ግንኙነቶች ነገሮችን ወደ መልካምነት መቀየር የሚያስደስታትና ለሰዎች ከራሷ በላይ የምታስብ አስባም የሚሳከላት ቆራጥ ሴት ናት፡፡ ለምታደረገውም ነገር በእረግጠኝነት የምትናገር ሲሆን ከምንም በላይ በራሷ የምትተማመን የወንዶችን ድጋፍ የማትሻ የማህበረሰቡ ቢሂል ወደኋላ የማይጎትታት አይበገሬ ናት፡፡ ልክ እንደምዕራባዊት ሁሉ ክልክላ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የምናገኛት ዋና ገጸባህሪ ምንትዋብ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በበላይነት የምትሳተፍ ስትሆን ስለሴቶች ያለውን የተዛባ አስተሳሰብ የምትቃወምና በተግባርም የምታሳይ እንስት ናት፡፡ ምንትዋብ ስለሴቶች የነበረውን የተወላገደ አስተሳሰብና ባህል ጨፍልቃ የያዘች የለውጥ ተምሳሌት ናት፡፡

እንደTyson (1999)  ወንዶችን ጠንካራና ወሳኝ አድርጎ የማየት እና የመፈረጅ በተቃራኒው ደግሞ ሴቶችን ደካማ እና የቤት ውስጥ ሥራ ብቻ የሚሰሩ አድርጎ የመቁጠር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሴቶች ለአመራር እና ለውሳኔ ሰጭነት ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነ ትገልጻለች፡፡ እስከ አሁን ባለው የሥነጽሑፍ ዳሰሳ ሴቶች የወንዶችን የበላይነት መዋቅር በባህላቸው እና በዕምነታቸው አስተምህሮ ውጤት መሰረትነት አምነው መቀበላቸውን የሚያሳዩ ሲሆን ይህም ሴቶች የተጨቆኑና በተጽዕኖ ውስጥ እንደነበሩ የሥነጽሑፍ ታሪኮች ይመሰክራሉ፡፡ ነገር ግን ምንትዋብ ለባህሉም ይሁን ለዕምነቱ የተሳሳተ ዕይታ ተገዢ ሳትሆን በችሎታዋና በብቃቷ የምትተዳደርና በስሯም በርካታ ሰራተኞችን የምታስተዳድር ናት፡፡ ማሳያ ብንመለከትም፡-

ወደ አራት ተኩል ወይ አምስት ሰዓት ከምሽቱ አካባቢ መኖሪያ ቤታቸው ይመጣሉ፤ ወርቂ ወይም መታሰቢያ ዋናውን በር ከፍተው ይቀበሏቸዋል፤ መታሰቢያ ቦርሳቸውን ተቀብላ ይዛ ከኋላ እየተከተለቻቸው ምኝታ ቤት ትገባለች፤ የኮሚዶዋ ቁልፍ ከቦርሳቸው ኪስ ታወጣና ቦርሳቸው ውስጥ በጥቁር ፌስታል ጠቅልለው ይዘውት የመጡትን ገንዘብ  ኮመዲኖው ውስጥ ታስገባለች፡፡

> እሱን ስትጨርስ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ለማቀበል ምንትዋብን ተከትላ መታጠቢያ ቤት ትገባለች፤ ከዚያ ሲወጡ የሌሊት ልብስ ታቀርባለች፤ እግራቸውንና እጃቸውን በሎሽን አሽታላቸው ፊታቸውን የሚቀቡትን ክሪም ታቀርባለች፤ […] ለአራቱም ንግድ ቤቶቻቸው የሚያስፈልገውን ሁሉ አቀናጅተው አቀራርበውና ሰራተኛ አሰማርተው ሲጨርሱ <u>ተኝቶ ከሚጠብቃቸው ፍቅረኛቸው</u> ጋር ቁርሳቸውን ለመብላትና ቡና ለመጠጣት ወደቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣ 30)፡፡

ምንትዋብ ቤተሰቡን ከመምራትና ከማስተዳደር ጀምሮ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች በንቃት በመሳተፍ አራት የንግድ ድርጅቶችንም በበላይነት ይመራሉ፡፡ ምንትዋብ ሴቶች ለቤት ውስጥ ስራ የተፈጠሩ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ የማይቀበሉ፤ ታናሽነትንና መሸነፍን የማይወዱ ጠንካራ ገጸባህሪ ናት፡፡ ማህበረሰቡ ለወንዶች ብቻ ሲሰጣቸው የቆየውን የስራ መሪነት በሴቷ ሲመራ ይታያል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በቤቷ ውስጥ ተኝቶ አልጋ ሲያሞቅ የሚቆያት ግርማ ልፍስፍስና የእሷን እጅ አይቶ የሚያድር ጥገኛ መሆኑን ከአስረጂው መረዳት ይቻላል፡፡ በቤታቸው ውስጥ ያሉ ሰራተኞች የስራ ክፍፍል እና እንክብካቤ የምንትዋብን ክብርና ግርማ ሞገስ የሚያሳይ ነው፡፡ ምንትዋብ በተለያዩ ዘረፎች ሴቶች ከወንዶች በተለየ የመስራት አቅምና ሙያ የሌላቸው ተደርገው በመቆጠር እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረጋቸውን እሳቤ በተግባር ሆና በማሳየት ውድቅ መሆኑን አሳይታለች፡፡

Demnile (1989) እንደገለጹት የሴቶች ንቅናቄ ዓላማ ሴቶችን ከአስቸጋሪ ህይዎት በማላቀቅ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን የበታችነት ደረጃ ማስቀረት ነው፡፡ ይህም የሥነጽሁፍ ሥራዎች እንደሚያመለክቱት ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች በመሰማራት ውጤታማነታቸውን አሳይተዋል፡፡ ምንትዋብ መብትና ግዴተዋን ጠንቅቃ የምታውቅ፣ አልቀበልም የሚል ካለ አስከሀይል ርምጃ ድረስ በመሄድ መበለጥን የማትሻ እንስት ናት፡፡ በአስረጅ ስንመለከትም፡-

> በፖሊሱ ውጤት አልባነት ላይ የግርማ አዋቂ ነኝ ባይነት ተደምሮ ትዕግስታቸውን ሲፈትነው ከተቀመጡበት ብድግ አሉ፡፡ “መጀመሪያውኑም አንተ ፖሊስ ጠራህብኝ እንጂ እኔ ምንትዋብ አበጀ <u>ከመከነ የፍትህ ስርዓት ፍትህ አልጠብቅም፡፡</u> መቼም ቢሆን በእራሴ አቅም መብቴን ማስከበርን አስቀድማለሁ፡፡ አሁንም ቶሎ ይፍታልኝና የማደረገውን አውቃለሁ አሉ፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣ 52)፡፡

ምንትዋብ ልክ እንደእሷ ሁሉም ሰው በስራው ብቁና ውጤታማ እንዲሆን የምትፈልግ ናት፡፡ ይህ እምነቷ ካልተሳካ ግን በውስጧ ሰላም የማይሰማትና ሰው የስራውን ማግኘት እንዳለበት የምታምን ቆራጥ ገጸባህሪ ናት፡፡ ለዚህም ነው ግርማ ነገሮችን ለማድበስበስ የሚያደረገውን ሙከራ ውድቅ በማድረግ በራሷ ማድረግን የመረጠችው፡፡ በሌላ መልኩ የግረማ አዋቂነት ባይነት ያናደዳት ምንትዋብ ከእሷ በላይ እበልጣለሁ የሚል ሰው ስለማትቀበል ነው፡፡ በተጨማሪም ከመከነ የፍትህ ስርዓት ፍትህ አልጠብቅም፡፡ መቼም ቢሆን በራሴ አቅም መብቴን ማስከበርን አስቀድማለሁ፡፡ አሁንም ቶሎ ይፍትሉኝ እንጂ የማደረገውን አውቃለሁ በማለት የምትናገርው የፍትህ አካላት በአግባቡ እና በሀቀኝነት ማህበረሰቡን ማገልገል አለመቻላቸውን ለማሳየት የተጠቀመችበት ነው፡፡

ምንትዋብ ጥገኝነትን የማትሻ መንፈሰ ጠንካራ ሴት ናት፡፡ ለዚህም ማሳያው፡-

‹‹ድሮም ህመም ይዞኝ እንጂ እኔ ምንትዋብ አበጀ አስቢ ተብዬ የምመከር ሰው አልነበርሁም፡፡ በየቀኑ አዲስ አዲስ ሃሳብ እያሰብሁ መተግበር እንጀራዬ ነው!›› ብለው ከፈገግታ ጋር አቆሙ፡፡ (ክልከላ፣239)፡፡

የምንትዋብ ጥንካሬ ህመም እንኳን የማይገድበው ሲሆን ነገሮችን በተግባር ማሳየት የምትችል በስራዋም የማትበገር የማህበረሰቡ ዋስትና የሆነች እንስት ናት፡፡ በአጠቃላይ ምዕራባዊትም ሆነች ምንትዋብ በማህበረሰባዊ ጉዳዮች ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች በንቃት የሚሳተፉና የሚሳካላቸው በዓባዊ ስርዓቱ ላይ ተጽዕኖ ማድረስ የቻሉና በማህበረሰቡ ዘንድ የነበርውን የተሳሳተ ግንዛቤ ያከሸፉ ሴቶች መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 3.2.1.3. የመደብ ተጽዕኖ

መደብ ተመሳሳይ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ በአጠቃላይም በሰው ልጆች አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ተመሳሳይ ማንነት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚመለከት ነው፡፡ በእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከልም ተጽዕኖ በማሳደርና ልዩነትን በመፍጠር ግለሰብን ከግለሰብ፣ ማህበረሰብን ከማህበረሰብ ነጥለው ለማየት የሚያስችሉ እንደ ትምህርት፣ ሙያ፣ የገቢ መጠን፣ ስልጣን፣ ዘር፣ ውበት፣ ገንዘብ በአጠቃላይም የኑሮ ደረጃ ቁልፍ ሚና ይጫዎታሉ፡፡ በዚህ ዘርፍ የሚታየውን ኢ-ፍትሃዊነት ደግሞ የማርክሲዝም ንድፈሃሳብ የትኩረት ነጥብ ነው፡፡ የማርክሲዝም ንድፈ ሃሳብ ወንዶች ሴቶችን ጉልበታቸውን እየበዘበዙ መክፈል የሚገባቸውን ደሞዝ በአግባቡ አለመክፈልና ሴቶች አቅም የላቸውም በሚል አስተሳሰብ ሴቶችን መጨቆን ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በምዕራባዊት እና በክልከላ ረጅም ልቦለድ ውስጥ

ስንመለከተው ወንዶች በሴቶች ላይ ጭቆና ያደርሳሉ የሚለውን በመቃረን ሴቶች በወንዶችና በራሳቸው በሴቶች ላይ የተለያዩ ጭቆናዎች ሲያደርሱ ይስተዋላል፡፡ በአስረጅ ስንመለከትም፡-

> እኔ እንደሚገባኝ አንድ ሰው መከራውን በልቶ ትምህርት የሚማረው ገንዘብ ለማግኘት ነው፡፡ ጥሩ ገንዘብ አግኝቶ ኑሮውን ለመለወጥና በሰወች ዘንድ ተቀባይነቱን ከፍ ለማድረግ እኔ ደግሞ በትምህርት መልፋት ሳይጠበቅብኝ እራሴን ብቻ ሳይሆን ልጆቸንና የልጅልጆቸን ጭምር አንቀባሮ የሚያኖር ሀብት ያለኝ ሰው ነኝ፡፡ ስለዚህ መማር ግድ የሚሆነው ለእኔ አይነቱ ሳይሆን ለእንደአንቺ አይነቱ ነው፡፡ ከቤተሰቦቹ ከስማቸውና ከድህነታቸው በስተቀር ምንም የሚወርሰው የሌለው ሰው የሚቀረው አማራጭ ትምህርት ብቻ ነው፡፡ ገባሽ! ነገሩ እንዴት ይገባሻል!"… (ክልከላ፣5)

ይህ አስረጅ የሚያሳየው ትርሲት የሃብታም ልጅ መሆኗን መታሰቢያ ደግሞ ድሀ መሆኗን ለማሳየት የተጠቀመችበት ማሸማቀቂያ ነው፡፡ መታሰቢያ ትምህርት ገብታ እንዳትማር የሚያግዛት ዘመድ አለመኖሩን ታውቃለች፡፡ በትርሲት ቤተሰብ ውስጥ ያለምንም ክፍያ በነጻ ጉልበቷን እየበዘበዙ እያሰሯት ትኖራለች፡፡ ትርሲትም በዚህ ደካማ ጎኗ ገብታ የበታች አድርጋ ስታሸማቅቃት እናያለን፡፡ ተጨማሪ ማሳያ ስንመለከትም፡-

> በግምገማ አይን ከላይ እስከታች አይቷት "አቤቱ! አሁን ይህንን ንግግርሽን የሰማ ሰው አዋቂ ትመስይዋለሽ፡፡ መልክና ወሬ ብቻ! ይህንን ቁመናሽን አይቶ የሰለጠነ የሚመስል ንግግርሽን የሰማ ሰው <u>ባለደረጃ ሴት</u> ትመስይው ይሆናል፡፡ አንች ግን ከይሉኝታና ከፍርሀት እስር ያልተፋታሽ <u>ባላገር</u> ነሽ! እኔ እንኳን ይህንን ጊዜ ያለፈበትን አስተሳሰብሽን ለመለወጥ ስንት ለፋሁ፡፡ <u>የሆንሽ ውሀ ወቀጣ ነገር ነሽ፡፡</u> ደሞ ነውር ትያለሽ? ነውርስ ለአላማ ስኬት ድንጋይ የሚፈነቀልበትን እድሜሽን ትርሲትን የመሰለች ተራ ሴት ስታገለግይ ማሳለፍ! ስሚ የወደፊቱ ደግሞ ከዚህም የከፋነው የሚሆነው፡፡ ወይ በትምህርትሽ አልገፋሽ፤ ወይ ቁንጅናሽን በጊዜው አልተጠቀምሽበት፤ ወይ ገንዘብ አላጠራቀምሽ፤ ዝምብለሽ የሴቶችን <u>ሽንት ቤት</u> ታጸጃለሽ፡፡" (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣13)፡፡

ግርማ እንደዚህ ደፍሮ በሴትነቷ የሚናገራት ጋብቻውን ፈጽሞ የምንትዋብን ሀብት እሱ እንደሚያስተዳድረው ፍላጎቱና ምኞቱ ስላለ ነው፡፡ የነገው ደግሞ የባሰነው የሚላትም በምንትዋብ ንብረት ላይ ባለሙሉ መብት ሲሆን የምንትዋብን ልጅ ትርሲትንና ቤት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩትን ሁሉ በምኞት የበቀል ሀይሉን ሊያሳርፍ የሚመኘውን ነው፡፡

ለምንትዋብ እዚህ ደረጃ መድረስ መታሰቢያ ትልቁን ሚና ብትጫወትም ከምትበላው ውጭ ለምትሰራው ስራ የሚከፈላት ቅንጣት ደሞዝ እንኳን የላትም፡፡ ይህም ሳያንስ በነጻ ማገልገሏ እንደነውር ተቆጥሮ እንደሚከተለው ይሳለቁባታል፡፡

> እንደአንች አይነቱ <u>የሰው ባሪያ</u> ከሚኖርበት ቤት ዙሪያ ውጭ ሌላ አለም ያለ አይመስለውም፡፡ እድል ድንገት ከዚያች ክልሉ የሚያወጣ አጋጣሚ ብትሰጠው እንኳን <u>አየር ያጥረዋል፡፡</u> ትንፋሹ የሚመለስለት ተመልሶ እራሱን እዚያው <u>ባርነቱ ቀንበር ስር</u> ሲያገኘው ነው፡፡ እናንተ <u>ባሮች</u> ትጋታችሁ ሁሉ <u>ያች የለመዳችኋት ኑሮ እንዳትለወጥ ነው፡፡</u> ምክንያቱም ደግሞ አንች እንደምታስቢው ጥሩ ሰዎች ስለሆናችሁ ሳይሆን <u>ሰነፎች ስለሆናችሁ እና አዲስ ነገር የመሞከርም ሆነ የመልመድ ብርታት ስለሌላችሁ ነው፡፡</u> ይልቅ እኔ ዋና ምክር ልምከርሽ!! ከእኔ ወገን ሁኝና ምንትዋብ እንድታገባኝ አሳምኝልኝ፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣15)፡፡

የምንትዋብና የሰራተኞችን የአኗኗር ዘይቤ ስንመለከት አንዳንዶች ከዚህ ግባ የማይባል ክፍያ ሲከፈላቸው አንዳንዶች ደግሞ ምንም ክፍያ የሌላቸው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለምሳሌ መታሰቢያን ስንመለከት የሚከፈላት ደሞዝ ባለመኖሩ የምትቀይረው ልብስ አጥታ ስትቸጋገር እናያታለን፡፡ ከተማ ሰው ለማግኘት ፈልጋ ከልጅየዋ ትርሲት ሳጥን ሙሉ ልብስ አንዷን ለብሳ ስትወጣ ትርሲት በእናቷ  እና በአክስቷ ፊት ለምን ልብሴን ለበስሽ በሚል ስትከሳት እናያለን፡፡ ትርሲት እራሷን የከበርቴ ልጅ አድርጋ ስለምትቆጥር በመካከላቸው ልዩነት ለመፍጠር ለምን ተደፈርሁ በሚል አስተሳሰብ አገር ይያዝልኝ ስትል ይስተዋላል፡፡ ይህም ከፍተኛ የሆነ የመደብ ጭቆና የሚደረግ መሆኑን ያሳያል፡፡

ምንትዋብ በሰራተኞቿ ላይ ከፍተኛ የሆነ የጉልበት ብዝበዛ ብቻ ሳይሆን አዕምሯዊና ስነልቦናዊ ጫናም ጭምር በከፍተኛ ደረጃ የምታደርስ አምባገነናዊ ሴት ናት፡፡ ለዚህም አስረጅነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> አንቱ ስራዎት ምንድን ነው! ከወጥ ቅቀላና ልብስ አጠባ ያወጣሁዎት እኮ ልጄን በስርዓት እንዲከታተሉልኝ ነው እንጂ እርስዎን <u>እመቤት</u> ማድረግ አምሮኝ አልነበረም፡፡  ለመሆኑ ይቺ ልጅ የት እንደምትውል እና የት እንደምታድር ማወቅ የለብዎትም? ይናገሩ እስኪ? አሉ የሚችሉትን ሁሉ ጉልበት አክለው፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣18)፡፡

ምንትዋብ ከጥበቃዎች ጀምሮ በሌሎች ሰራተኞች ላይ የምታሳየው ባህሪ ከንግግሯ  አንስቶ እስከ ተግባሯ ድረስ የጭቆና ሁኖ እናገኘዋለን፡፡ ምንትዋብ ራሷን በወንዶችም ሆነ በሴቶች ላይ ከፍ አድርጋ የምታይ ሌሎችን በስሯ ጨፍልቃ የያዘች ናት፡፡ ማሳያ እንመልከት፡-

> ምንትዋብ ትዕዛዝ ሲያስተላልፉ ወዲያውኑ አሉታዊ መልስ መስጠት የማይታሰብ ነው። ትዕዛዙ ሊፈጸም የማይችልበት በቂ ምክንያት ቢኖር እንኳን እሳቸው ዘንድ የሚቀርበው እያንዳንዱ መንገድ ተሞክሮ ሳይሳካ ሲቀር ‹‹ለምን?›› የሚል ጥያቄ ከራሳቸው ከመጣ ብቻ ነው። ምንትዋብ ለሰበብ አስባብ ያላቸውን ጥላቻ ሲገልጹ ‹‹ምክንያት ፈጣሪን ከመቆጣት፣ አዳምና ሄዋንን ከእርግማን አላዳናቸውም!›› ይላሉ። (ክልከላ፣16)።

ምንትዋብ በአገዛዟ አስፈሪና አምባገነናዊነትን የተላበሰች ሴት ናት። ከማስረጃዎች እንደምንረዳው ምንትዋብ ትዕዛዝ አዝዘው አሉታዊ ምላሽ ለዚያም የሚሆን ሰበብ ወይም ምክንያት የማይፈልጉ ናቸው። ለምንትዋብ ምላሽ መስጠት የማይችሉት የመጀመሪያው ምንትዋብ በማህበራዊም ሆነ በኢኮኖሚው መስክ የበላይ መሆኗን የሚያሳይ ሲሆን ሌላው ደግሞ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሰራተኞች የራሳቸውን ማንነት ከምንትዋብ ማንነት እንደሚያንስ አምነው መቀበላቸውን አመልካች ነው። ስለዚህ መደብ ወንዶች በሴቶች ላይ ከሚደርሰው በተቃራኒ ሴቶች በወንዶች ላይ እና ሴቶች በሴቶች ላይ የሚያደረሱትንም ተጽዕኖ አመልካች ነው። ትዕዛዙ ሊፈጸም የማይችልበት በቂ ምክንያት ቢኖር እንኳን እሳቸው ዘንድ የሚቀርበው እያንዳንዱ መንገድ ተሞክሮ ሳይሳካ ሲቀር ‹‹ለምን?›› የሚል ጥያቄ ከራሳቸው ከመጣ ብቻ ነው። የሚለው ማስረጃ የሚያስረዳው ምንም እንኳን አጥጋቢ ምክንያት ቢኖራቸውም ከምንትዋብ ለምን የሚል ጥያቄ ካልመጣ በቀር መናገር አለመቻላቸውን ነው። ይህም የሚያሳየው የምንትዋብ ሰራተኞች የመናገር መብት እንኳን አለመኖራቸውን ነው። ሁሉም ነገር በምንትዋብ ቁጥጥርና ሀላፊነት እንደሆንም የስገነዝባል። ስለዚህ የመደብ ጭቆና በወንዶችም ይሁን በሴቶች ያልቀረ ሲሆን ሴቶች በሴቶችም ያለቸውን ተጽዕኖ ያሳያል። የመደብ ተጽኖውም የመናገር መብታቸውን እንዳሳጣቸው ያስርዳል።

Banks (1999) እንደሚገልጸው መደብን ለመወሰን ከሚያስችሉ ጉዳዮች ውስጥ አብዛኛዎቹ የገቢ መጠን፣ ትምህርት፣ ስራ፣ የኑሮ ደረጃና እሴቶች /values/ ናቸው፤ በማለት (Warner 1960) ጠቅሶ ያስረዳል። በዚህም መሰርት የምንትዋብ ዘመዶች ሳይቀሩ እህታችውን የሚመጥን ወንድ እንዳሌለ አድረገው ይቆጥራሉ። ማስረጃ እንመለከት፡-

> በትጋታቸው፤ በሃብታቸው ብዛት፤ በአለባበስና ንግግር አዋቂነታቸው፤ በለጋስነታቸውና በመልከመልካምነታቸው የተነሳ በቤተሰቦቻቸው ዘንድ ከፈጣሪ ዝቅ ብለው የሚመለከቱት ምንትዋብ አበጀን የሚመጥን ወንድ አለ ብሎ የሚያምን ሰው የለም። በዚህ የተነሳ ከጀረባው የቆመ ሀብትም ሆነ ንብርት

> የሌላው ግርማ በሁሉም ሰው ዘንድ በጥቅም ፈላጊነት ተመዝግቦ ቆይቷል፡፡ (አጽንኦቱ የእኔ፤ ክልከላ፣147)፡፡

በመደብ የተከፋፈለ ማህበረሰብ የሴቶች ጭቆና መሰረት ያደረገ ቢመስልም ውጤቱ ግን አባዊ ሥርዓት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል በማለት Madsen (2000) የምትገጽ ሲሆን ከሃሳቡም የመደብ ልዩነትን የተለያዩ ጉዳዮች ቢፈጥሩትም በውስጡ የአባዊ ስርዓት ተጽዕኖ መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡

የመደብ ተጽዕኖ በሴቶች ላይ ሲደርስ የቆየ ቢሆንም በምንትዋብ ዘመዶች የሚታየው ግን በተቃራኒው በሴቷ የሀብት ብዛት ምክንያት በወንዶች ላይ የሚደርሰውን የመደብ ተጽዕኖ ነው፡፡ ምንትዋብ በሀብት ደረጃ ማንም የማይወዳደራት ስትሆን በቤተ ዘመዱም ላይ ከእግዚአብሄር ቀጥሎ እንደ ትልቅ ባለ ጸጋ የምትቆጠር ጠንካራ ሴት በመሆኗ የእሷን ደረጃ የሚመጥን የትዳር አጋር ካልሆነ ማግባት እንደማትችል ውስጣቸውን አሳምነውታል፡፡ በዚህ መሰርት ግርማ ለምንትዋብ የማይመጥን ወንድ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ይህም እንዲሆን ያደረገው የሀብት ደረጃቸው የማይመጣጠን ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ የሀብት ደረጃ የመደብ ልዩነት የሚፈጥር ሲሆን ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ወንዶች በሴቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ሳይሆን ሴቶች በወንዶች ላይ የመደብ ተጽዕኖ የሚያደርሱ መሆኑን ያሳያል፡፡

የመደብ ልዩነት በሰዎች ላይ በተለያየ መልኩ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ የሞራል ውድቀትና ስነልቦናዊ ችግር መፍጠሩ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ እንመለከት፡-

> ‹‹ግልጽ አይደለም እንዴ! ልታናግርህም ሆነ ልታይህ አለመፈለጓ የሚያስተላልፍልህ ምንም መልዕክት የለም? ይችን ያህል ማገናዘብማ ከማንኛውም ሰው ይጠበቃል እኮ፡፡ በጥዋቱ ቅመህ መርቅህ ከሆነ ደግሞ በረድ ሲልልህ ተመልሰህ ና እና እሷን ትተህ <u>በደረጃ የሚመጥንህን ሰው</u> እንድትፈልግ እንደገና እነግርሃለሁ፡፡›› አለችው በአጽንኦት፡፡ ሳምሶን ከፋው፡፡ “ደረጃ ስትይ ገንዘብ ማለተሽ ነው?” አለ ቅሬታው እየታወቀበት፡፡ (አጽንኦቱ የኔ፤ ክልከላ፣198)፡፡

አብነት ለሳምሶን የምትናገርው ንግግር የመደብ ልዩነትን አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ እንደ አብነት አገላለጽ ለማናገርና ለማየትም በመደብ ወይም በደረጃ ተመመሳሳይ መሆን መቻል እንዳለበት አስረጂ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ልታናግርህም ሆነ ልታይህ አለመፈለጓ የሚያስተላልፍልህ ምንም መልዕክት የለም? የሚለው አስረጂ በተዘዋዋሪም ቢሆን አንተ ለትርሲት አትመጥንም ለማለት የተጠቀመችበት ነው፡፡ በተጨማሪም በደረጃ የሚመጥንህን ሰው እንድትፈልግ እንደገና

እነግርሃለሁ የሚለው የአብነት አገላለጽ በሀብት ዝቅ ያለ ሰው ሀብታም ወይም የሀብታም ልጅ ማፍቀር አይችልም የሚል አንድምታ አለው፡፡

የቆየው አመለካከት የሁሉም ሴቶች ኢኮኖሚ በወንዶች ላይ ጥገኛ የሆነና በወንዶች የሚመራ ነበር:: ይህም የመደብ ልዩነት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በቀደምት የሥነጽሁፍ ስራዎች ውስጥ የመደብ ልዩነት ተጽዕኖ የሚፈጠረው ወንዶች በሴቶች ላይ ነበር፡፡ ይህም ተጽዕኖ ሴቶችን ለዘመናት ሲጨቁን ቆይቷል፡፡ በክልከላ ረጅም ልቦለድ ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ምንትዋብ የተሰኘችው ዋና ገጸባህሪ በወንዶች ላይ ብቻ ሳይሆን በሴቶች ላይ ጭምር የመደብ ተጽዕኖ በማድረስ ጉልበታቸውን ስትበዘብዝ ያሳያል፡፡ ማስረጃ እንመለከት፡-

> መታሰቢያ እንደ ሌላው ጊዜ አጠገባቸው ቆማ፣ ልብሳቸውንና መጊያጊያጫቸውን እያነሳች ስታቀብላቸው ሲያዩ ብስጭታቸው እንደአዲስ አገርሽቶ የሚያደርጉት ቸገራቸው፡፡ <u>ደሞዝ ቢኖራት ደሞዟን ይቆርጡ ነበር፣ እያስፈቀደች ከቤት የምትወጣበት ፕሮግራም ቢኖራት እሱን በመከልከል ይበቀሏት ነበር፡፡</u> ሊሰጧት ያዘጋጁት ስጦታ ቢኖራቸው እሱን በማስቀረት አንጀቷን ያሳርሩት ነበር፡፡ ይሄ ሁሉ ባለመኖሩ ለጥፋቷ ዋጋ የሚያስከፍሉበትን ስልጣን እጃቸው ላይ አጡ፡፡ እስከ አሁን እያደረጉት ያለው ፊት መንሳትና ንግግራቸውን መወሰን በቂ ቅጣት አልሆነላቸውም፡፡ (አጽንኦቱ የኔ፣ ክልከላ፣50)፡፡

መታሰቢያ ለበረካታ ጊዜያት ያሳለፈችው በምንትዋብ ቤት የቤት ውስጥ ስራዎችን በመስራት ነው፡፡ በስራዋም ክፍያ ሳይኖራት ያለ በቂ እረፍት ምንትዋብን በባርነት ስታገለግል የምትኖር ናት፡፡ ምንትዋብ በሀብቷ በመመካት ወንዶችንም ሆነ ሴችን ጉልበታቸውን ትበዘብዛለች፡፡ ሌሎች ደሞዝ የሚከፈላቸው ሲሆኑ መታሰቢያ ግን በተለየ በረካታ ስራ እየሰራች የምትለብሰው እንኳን የተሻለ ልብስ የላትም፡፡ ይህም የሚያሳየው የመደብ ተጽዕኖ በከፍተኛ ደረጃ የሚንጸባረቅ መሆኑን ነው፡፡ ሌላው የምንትዋብን አምባገነናዊ አገዛዝ አጉልቶ የሚያሳየው ያለምንም ደሞዝ ጉልበቷ የሚበዘበዝባትን መታሰቢያን ከዚያ የከፋ ጉዳት ለማድረስ የምታደርገው ጭካኔ ሴቶች በሴቶች ላይም የሚያደርሱትን የመደብ ጥቃት አመላካች ነው፡፡

ምንትዋብ ብቻ ሳትሆን እሷን መከታ ያደረጉት ልጇ እና እንደእጮኛ ነኝ ብሎ የቀረበው ነገር ግን ሃብቷን ለመብላት ብሎም ለመውረስ የተጠጋት ግርማ ሳይቀር ሰራተኞች ለሚሰሩት ስራ ምስጋና ወይም ክብር ሳይሰጡ ለሆዳቸው ሲሉ የሚገዙ በማስመሰል ሲሰድቧቸው እናያለን፡፡ አስረጅ እንመልከት፡-

"የሚጠጣ ትኩስ ነገር ላምጣልህ ጋሽ ግርማ? ሻይ፤ ቡና ወይም ወተት?" አለችው፡፡

"ትኩስ ነገርሽ ይጥፋ! እኔ ስለአንቺ ህይዎት እጨነቃለሁ፤ አንቺ አሁንም ስለባርነት ነው የምታስቢው፡፡ ቆይ ምንድን ነው እንደዚህ ያደነዘዘሽ?" አለ ተቆጥቶ፡፡ መታሰቢያ አሁንም ትንሽ ወደኋላ አፈገፈገች፡፡ (ክልክላ፣14)፡፡

አስረጅው የሚያሳየው ግርማ የተሰኘው ገጸባህሪ ዕጮኛውን መከታ በማድረግ አሱም በተራው በእነዚህ ባልታደሉ ምስኪን ሰራተኞች ላይ የበላይነቱን ለማሳየት በመዝለፍና በማሽማቀቅ ስነልቦናዊ ጫና የመፍጠር ስራ እየሰራ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶች በወንዶችና በሴቶች እንዲሁም ወንዶች በሴቶች ላይ የመደብ ተጽዕኖ የሚያደርሱ መሆኑን ነው፡፡

ከለይ መደብን ስለሚወስኑት ነገሮች ሲነሳ ለራሳችን የሚሰጥ ክብርና ለሌሎች የሚሰጥ ክብር አንዱ እንደሆነ ተወስቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተዛመደም ወርቂ የተሰኘችው የምንትዋብ ሰራተኛ የራሷን ማንነት ዝቅ በማድረግ የሌሎችን ከፍ በማድረግ እሷ የማትረባ መሆኑን በራሷ አንደበት ትናገራለች፡፡ ለዚህም ማሳያ፡-

"እርግጥ አንቺ ብዙ የተማርሽና ብዙ የምታውቂ ልጅ ነሽ እኔ ደሞ ምንም ያልተማርሁና እትዬን ከማገልገል በስተቀር ሌላ የሚረባ እውቀት የሌለኝ ሰው ነኝ፡፡" (አጽዕኖቱ የኔ፤ ክልክላ፣74)፡፡

ይህ ንግግር የሚያሳየው ወርቂ ራሷን የበታች አድርጋ የሌሎችን ደግሞ ከፍ በማድረግ ራሷን ከሰራተኛነት ውጭ ሌላ አለም የሌላት እንደሆነ አምና የተቀበለች መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ የሚዳርጋቸውም የገንዘብ እጥረት ስለሚያጋጥማቸው፣ የተሟላ የትምህርት እድል ስለማያገኙ፣ ራሳቸውን ዝቅ ስለሚያድርጉ፣ በሚሰሩት የጉልበት ስራ በቂ ገንዘብ ስለማይከፈላቸው በተጨማሪም በአሰሪዎቻቸው ዘንድ የበታችነታቸውን የሚያጎሉ ንግግሮችን ስለሚናገሯቸው ነው፡፡ በአጠቃላይም ይህ ሁሉ ተደማምሮ አሁንም ድረስ በሴቶችም ይሁን በወንዶች ላይ የመደብ ተጽዕኖ እንዳለ ከማስረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- ማጠቃለያ እና መደምደሚያ

## 4.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የዓባዊ ሥርዓት ተቃውሞ በአሰፋ በቀለ *ምዕራባዊት* (2004) እና በዮርዳኖስ ሽፈራው *ክልክላ* (2010) ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚል ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተመረጡትን ልቦለዶች ከአንስታይ ሂስ ንድፈ ሃሳብ አንጻር መመርመር ነው፡፡ አጥኚው ዋና ዓላማውን ለማሳካት በልቦለዶቹ ውስጥ የሚስተዋሉ የሴትነት ጉዳዮችን በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ እና የመደብ ተጽዕኖን ከአባዊ ስርዓት አንጻር መተንተን የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎች ተጠቅሟል፡፡

በትንታኔው መሰረት በልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙ ሴት ገጸባህሪያት የአባዊ ሥርዓቱን በመጣስ የኢኮኖሚውን ዘርፍ ሲቆጣጠሩትና በበላይነት ሲመሩት ይታያል፡፡ በክልክላ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የምትገኘዋ ዋና ሴት ገጸባህሪ ምንትዋብ የብዙ ድርጅቶችና ሃብቶች ባለቤት ስትሆን በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ ባሉ ስራዎች የመሪነትና የአስተዳዳሪነት ሚናን እንደምትዎጣ ትንታኔው ያሳያል፡፡ በምዕራባዊት ረጅም ልቦለድ ውስጥም ምዕራባዊት የተባለችው ዋና ገጸባህሪ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር የጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሀላፊ ስትሆን በስራዋ ጠንካራና ታታሪ በመሆኗ ለሌላ ድርብ ሀላፊነት ጭምር የምትመረጥ ገጸባህሪ ናት፡፡ በሁለቱም መጽሃፍት የሚገኙት እንስት ገጸባህሪያት ሴቶች መምራትና ማስተዳደር አይቹሉም የሚለውን የማህበረሰቡ አስተሳሰብ በማስወገድ ሴቶች በየትኛውም መስክ ተሰማርተው መስራት ብቻም ሳይሆን በብቃት የመምራትና የማስተዳደር አቅም እንዳላቸው በተግባር አሳይተዋል፡፡

የማህበራዊ ተሳትፏቸውን ስንመለከትም በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት የሚሳተፉና በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን የቆየና የተሳሳተ አስተሳሰብ በመሻር ዋና ዋና ሀላፊነቶችን እየወሰዱና መስዋዕት እየከፈሉ የተበተነ ቤተሰብን ሲያስታርቁ ይስተዋላል፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ሴት ገጸባህሪያት በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የእርስበዕርስ ግንኙነት ያላቸውና በርካታ ድርጅቶችንና ቤተሰባቸውን በብቃት የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ናቸው፡፡ ሌላው ሴቶቹ ከጥገኝነት የተላቀቁና ምክንያታዊ የሆኑ አስተሳሰቦችን በመያዝ መብታቸውን የሚያስከብሩ ቆራጥ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ለበርካታ ዘመናት ሴቶች የፈለጉትን እንዳያገቡ አባዊ ስርዓቱ ተጽዕኖ ሲፈጥርባቸው ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በነዚህ በተመረጡት

ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ሴት ገጸባህሪያት ዓባዊ ስርዓቱን አሜን ብለው በመቀበል በወንዶች ተጽዕኖ ስር የሚወድቁ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በምዕራባዊት ረጅም ልቦለድ ውስጥ የምትገኘዋ ምዕራባዊት አካሉ የተሰኘውን ገጸባህሪ አግባኝ ብላ በመጠየቅ ስታገባው እናያታለን፡፡ በክልከላ ውስጥ ደግሞ ምንትዋብ አባዊ የሆነውን የጋብቻ ስርዓት በመጣስ በእድሜ ከእሷ በአስር አመት ከሚያንሰው ግርማ ጋር በፍቅር አብርው ሲሆኑ ይታያል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ልዩነት ስነሕይዎታዊ እንጅ ከመስራትና ከማግኘት ጋር ያልተያያዘ መሆኑን ነው፡፡

በሴቶች እና በወንዶች ላይ ገደብ በማበጀት ሴቶች እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ሲያደርግ የቆየው የመደብ ተጽዕኖ በክልከላና በምዕራባዊት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ሲታይ ወንዶች በሴቶች ላይ ሳይሆን ሴቶች በወንዶች ላይ እንዲሁም ሴቶች በሴቶች ላይም የመደብ ጭቆና እንደሚያሳድሩ ከትንታኔው ለማየት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ሲታይ ሴት ገጸባህሪያት በኢኮኖሚው እና በማህበራዊ ዘርፍ እንዲሁም ከመደብ አንጻር የዓባዊ ሥርዓቱን በመጣስ የመስራት አቅማቸውንና ጥንካሪያቸውን በተግባር ያሳዩ ገጸባህሪያት ናቸው፡፡

## 4.2. መደምደሚያ

በማጠቃለያው ማየት እንደተቻለው *ምዕራባዊትና ክልክላ* የተሰኙት ረጅም ልቦለዶች የዓባዊ ሥርዓቱን በመጣስ ስለሴቶች የነበረውን የተዛባ አመለካከት በመቀየር ሥነጽሑፍ ከጥበብነቱም አልፎ ለማህበረሰቡ ለውጥና እድገት የሚጫወተውን ሚና አጉልተው ማሳየት የቻሉ ሥራዎች መሆናቸውን ልቦለዶቹ ካነሷቸው ጭብጦች መረዳት ተችሏል፡፡

ልቦለዶቹ ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወስዱና ጥሩ የሆነ ተሳትፎ በማድረግ ጉልህ ሚና መጫዎት እንደሚችሉ አሳይተዋል፡፡ ሴቶች የቀረቡበት መንገድም ከእነሱም አልፎ ለወንዶች፤ በአጠቃላይም ለማህበረሰቡ ጉልህ ሚና እንዳላቸው መረዳት ተችሏል፡፡

ማህበራዊ ተሳትፏቸው ሲታይም “ሴት ወደማጀት ወንድ ወደችሎት” የሚለውን ስር ሰዶ የቆየ አስተሳሰብ ውድቅ በማድረግ አንኳር አንኳር በሆኑ ቦታዎችና የስራ ሃላፊነቶች ላይ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን በበላይነት በመምራትም ጭምር አይበገሬነታቸውን አስመስክረዋል፡፡

በአጠቃላይ ልቦለዶቹ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ በአጠቃላይም በባሕሉ ላይ የፈረጠመ ጡንቻውን ያሳርፈውን ዓባዊ ሥርዓት በማስወገድ ሴቶች በማንኛውም ዘርፍ ከወንዶች እኩል መስራት እንደሚችሉ በተግባር ማሳየት ችለዋል ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

***፩. ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች***

አሰፋ በቀለ፡፡ (2004)፡፡ *ምእራባዊት*፡፡ International Leadership Institute Printing Press.

ዮርዳኖስ ሽፈራው፡፡ (2010)፡፡ *ክልክላ፡፡* አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኀላ.የተ.የግ.ማህበር፡፡

**፪. ካልዓይ የመረጃ ምንጮች**

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም፡፡ (1978)፡፡ *ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስአበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ብርሃን አሰፋ፡፡ (2009)፡፡ "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች፡፡" ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ (ያልታተመ)፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001)፡፡ *በይነ ድሲፕሊናዊ የሥነጽሑፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

አጋረደች ጀማነህ፡፡ (ዓ.ም የሌለው)፡፡ "*ሴትነትና እናትነት በፀሐይ መለአኩ ልቦለዶች፡፡*" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ (*ያልታተመ*)፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (2002)፡፡ *የስነጽሁፍ መሰረታውያን፡፡* (5ኛ እትም):: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Abrams, L. (2001). Ideals of Womanhood in Victorian Britain. History Trails: Victorian Britain, 9.

Abreham Alemu. (2000). "Oral Narrative as Ideological Weapon for Subordinating Women: the case of Jimma Oromo." *Journal of African Cultural Studies*, Vol. 19, No. 1. 55-80. (http://dx.doi.org/10.1080/13696810701485934.

Banks, J. A. (2010). ‹‹Multicultural Education: Characteristics and Goals››. In J. A. Banks, and C. M. Banks. (Eds.). *Multicultural Education: Issues and Perspective* (7th ed.), Hoboken: John Wiley and Sons,Inc.

Barker, C. (2008). *Cultural Studies: Theory and Practice.* London: Sage Publications.

Barrett, M. (1980). *Women's Oppression Today: Problems in Marxist Feminist Analysis*. London: Verso Editions.

Belsey, C and Jane M. (eds.) (1897). The *Feminist Reade*r. New York: Palgrave Macmillan.

Bengsten, M. (1977). *Political Economy of Women's Liberation.* In A. Bierman, & J. A. Gould, Philosophy for a new Generation (pp. 461-466). New York: Macmillan. Publishing Co. Ltd.

Brown, C and Karen O. (1978). *Feminist Criticism: Essays on theory, Poetry and Prose.* New Jersey: The Scarecrow Press, Inc.

Eskinder Hailu. (2008). Female Rules and Sacrifice in Poltical Drama and Film. A Comparative study of Death and Maiden. and The Father From A Feminist Perspectives. (Unpuplished). MA Thesis. Addis Ababa; Addis Ababa University.

Evans, M. (1997). *Introducing Contemporary Feminist Thought:* Cambridge: Blackwell Publishing Ltd.

Fischer, A. Patricia M. and Vianen, A. (2004). "Gender and Culture Differences in Emotion." *Journal of American Psychological Association*. Vol. 4.1,87-94.

Joseph, G. and Jill. L. (1981). *Common Differences: Conflicts in Black and White Feminist Perspectives*, New York: Ancho.

Josephine, D. (1993). *Feminist Theory: The Intellectual Traditions of American feminism.* (2nd ed.) New york: continuum.

Julian, W. Ruth, R. and Kenneth, W. (2006). (2nd ed). *Key Concepts in Literary Theory*. Edinburgh University Press.

Julia, W. (2012). *Gendered Lives.* Boston: Cengage Learning. Print.

Keith, G. and Jille, B. (1996). *Critical Theory and Practice*. London and Nework; published by Routledge.

Madsen, D. (2000). *Feminist Theory and Literary Practice.* London: Pluto Press.

Phillips, A. (1993). *Democracy and Difference.* Cambridge: Polity Press.

Selamawit, Mecca. (2002). ``The Portrayal of Women in the Old Testament: A Feminist Reading of the Books of Susanna, Judith and Ruth.`` (Unpuplished). MA Thesis. Addis Ababa; Addis Ababa University.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today.* (2nd ed). Nework London. Routledg.

Tyson, L. (1999). Critical Theory Today. Nework London. Cambridge.

Vicinus, M. and Nergaard, B. (1989). *Ever yours, Florence Nightingale Selected Letters*. London: Virago Press.

Warhol, R. and Price H. (eds). (1991). *Feminisms: An Anthology of Literary Theory and Criticism,* New Jersey: Rutgers University Press.

Woolf, Virginia. (2012). *A Room of One's Own.* Florida: Houghton Mifflin Harcourt Print.

## ፫. የኢንተርኔት እና የድረ-ገጽ የመረጃ ምንጮች

"What is Social class?" Retrived on http://udel.edu/~cmarks/ What% 20is%2 0 social % 20 class.htm. from…

"Social class." Retrived on Wikipedia, the free encyclopedi, from (December 29 2017). https://en.wikipedia.org/wiki/Social_class.